# የዝናብ አጠር ስነ-ምህዳራዊ ግብርና ተሞክሮ በኮነባ ወረዳ (አፋር)






<u>አዘጋጆች</u>

- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)
- ምትኩ ሃይለ (ፕ/ር)
- ነፃነት ገነነ
- ብርሃኑ ሓጎስ
- ኑርሁሴን ከማል
- መሃመድ እድሪስ



ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ህዳር 2013 ዓ.ም.

# ኮነባ ወረዳ፡- የዝናብ አጠር ስነ-ምህዳራዊ ግብርና ተሞክሮ


**አዘጋጆች**

- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)
- ምትኩ ሃይለ (ፕሮፌሰር)
- ነፃነት ገነነ
- ብርሃኑ ሓጎስ
- ኑርሁሴን ከማል
- መሃመድ እድሪስ



ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም
ህዳር 2013 ዓ.ም.
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

**ህትመት**

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም እና ምርጥ ተሞክሮ ማህበር

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 171 ኮድ 1110፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር፡- +251-911-246046/978-815102

ፋክስ ቁጥር፡- +251-116-686724

ኢ.ሜይል አድራሻ፡- hailuara@yahoo.com

© ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም፣ 2013

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም ከምርጥ ተሞክሮ ማህበር ጋር በመሆን ይሄን የፕሮጀክት ሃሳብ በመሬት ላይ እንዲተገበር እና እንዲታተም የተደረገው በBread for the World/ PADD (ምግብ/ዳቦ ለዓለም) የገንዘብ ድጋፍ በመሆኑ ከፍ ያለ ምስጋናና አድናቆት ያቀርባል፡፡

መፅሃፍ አርታኢ፡- ሞገስ ሕሉፍ

የሽፋን ዲዛይን፡- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)

| ተ.ቁ | ቢጋር | ገፅ |
|---|---|---|
| 1. | **መግቢያ** ………………………………………………….. | 01 |
| 2. | **አጀማመር** ……………………………………………….. | 03 |
| 2.1. | የፕሮጀክት ተጠሪ ሆኖ መመደብ ………………………… | 06 |
| 2.2. | አዲስ ሃሳብ ……………………………………………….. | 07 |
| 2.3. | የትምህርታዊ ጉዞ የተደረገ ቅድመ-ዝግጅት ……………… | 09 |
| 3. | **የመጀመሪያው የትምህርታዊ ጉብኝት** ……………………. | 12 |
| 3.1. | የአርሶአደር ወ/ገብርኤል የልማት ስራ ክንውኖች ጉብኝት .. | 12 |
| 3.2. | የወ/ሮ ሃረጉ የእርሻ ስራ ጉብኝት ………………………… | 15 |
| 3.3. | የዓድሓ ቀበሌ የልማት ስራ ጉብኝት ……………………… | 19 |
| 3.4. | የችግኝ ፍላጎት እና ተከላ …………………………………. | 21 |
| 3.5. | የመረጃ ልውውጥ …………………………………………. | 22 |
| 4. | **ሁለተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት** ………………………. | 24 |
| 5. | **ሶስተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት** ……………………….. | 29 |
| 6. | **አራተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት** ………………………. | 33 |
| 6.1. | ታታሪ ሴት ከፊል አርብቶአደሮች ………………………… | 33 |
| 6.2. | የኮነባ ወረዳ የካቢኔ አባላት ……………………………….. | 34 |
| 6.3. | በኮነባ ወረዳ ውስጥ ጥሩ የስራ ተሳትፎ ያላቸው ወጣቶች… | 35 |
| 6.4. | የፔለም ኢትዮጵያ ታሳቢ አባል ድርጅቶች ……………….. | 36 |
| 6.5. | የተጎበኙ ቦታዎች …………………………………………... | 36 |
| 6.6. | ከትምህርታዊ ጉብኝቱ የተቀሰመው ትምህርት …………… | 37 |
| 6.7. | እንደ ማጠቃለያ የተደረጉ ውሳኔዎች …………………….. | 40 |
| 7. | **የፕሮጀክቱ ዘላቂነት ምን ይመስላል** ……………………. | 43 |
| 7.1. | የችግኝ አቅርቦት ቀላል እና ተደራሽ ማድረግ …………… | 43 |
| 7.2. | የቤተሰብ ተሳትፎ ማጠናከር ………………………………. | 44 |
| 7.3. | ወደ ዘላቂ የችግኝ አቅርቦት ጉዞ ከነ አማራጩ …………… | 54 |
| 7.4. | ለሩሕ ተፋሰስ ስራ የተደረገ ቅድመ-ዝግጅት ……………… | 67 |
| 7.5. | የኮነባ ወረዳ ካቢኔ አባላት ስለፈተፋሰስ ስራው ያስተላለፉት ውሳኔ ……………………………………………………… | 76 |
| 8. | **እውቅናና ሽልማት** ………………………………………… | 77 |
| 9. | **ማጠቃለያ እና አስተያየት** ……………………………….. | 80 |
| 10. | **የኮነባ ወረዳ ዋና ዋና ቀጣይ የቤት ስራዎች** …………… | 83 |
| 11. | **የምርጥ ተሞክሮ ስራ በምስል** …………………………… | 84 |

# ምስጋና

ፔለም ኢትዮጵያ ይህንን ውጤታማ ስራ ተከትሎ የተዘጋጀውን ህትመት በማስመልከት ለሚከተሉት የህብረተሰብ ክፍል፣ የመንግስት አካላት፣ ግለሰቦች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ላበረከቱት ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ልባዊ ምስጋናውን እንደሚከተለው ያቀርባል፡፡

አንደኛ እና ዋነኛው የኮነባ ወረዳ ከፊል አርብቶአደሮች በተለያዩ ምክንያቶች እነሱ ቦታ ላይ ይሰራል ተብሎ የማይገመተውን ውጤታማ የልማት ስራ በተግባር ሰርተው በማሳየታቸው ላቅ ያለ ምስጋና ያቀርባል፡፡

ሁለተኛ ይሄን ስራ እዚህ ቦታ ላይ ቢሞከር የተሻለ ይሆናል ብለው በመምከር እዚህ ወረዳ ላይ እንድንሰራ ምክራቸው ለለገሱን ፕሮፌሰር ምትኩ ሃይለ እና አቶ ሃፍቶም ውሬታ በተለይ ደግሞ ፕ/ር ምትኩ በየጊዜው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የስራውን ውጤታማነት ለማየት፣ ለመከታተል እና ምክር ለመስጠት ያደረጉት አስተዋፅኦ ምስጋና ያንሰዋል፡፡ ፔለም ኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ከጤና ጋር ይመኛል፡፡

ሶስተኛ የመንግስት አካላት እና ባለሙያዎች ላልተቆጠበ ሁለገብ አስተዋፅኦቸው ከፍ ያለ ምስጋና ሳቀርብ ደስተኛ ነኝ፡፡ ከዚህ ባልተናነሰ ደግሞ የሰመራ እና መቐለ ዩኒቨርሲቲዎች በተለይም ለፕ/ር ክንደያ ገ/ሂወት፣ ዶ/ር አብድራሕማን ከድር፣ ዶ/ር ይርጋ ወልዱ እና አቶ ማሕሙዳ … ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁኝ፡፡

በስተመጨረሻ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገው ዳቦ ለዓለም (Bread for the World) ሳመሰግን በተለይ ደግሞ የምስራቅ አፍሪካ ተወካይ ሚ/ር ክርስቶፍ ሽናይደር፣ ወ/ሪት ፅዮን ታደሰ፣ አቶ በቀለ ሙላት፣ አቶ ዳዊት ሰለሞን፣ ወ/ሪት ትግስት ወንድምአገኘሁ፣ ወ/ሪት ኤልሳቤጥ ዓለም እንዲሁም የድርጅቱ ሰራተኞች ላደረጉልን ሁለገብ ድጋፍ፣ ማበረታቻ እንዲሁም የመስክ ጉብኝት ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁኝ፡፡

ሃይሉ አርአያ ተድላ (ዶ/ር)
ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም
አዲስ አበባ

## መቅድም

ይህ ፅሁፍ የሚያትተው በከፊል አርብቶ አደር አካባቢ የተደረገ የስር-ነቀል ለውጥ ነው፡፡ የኮነባ ማህበረሰብ በአካባቢው ያሳየውን ስኬታማ ስራ፣ ፈጠራ እና ችሎታን ለማሳየት ሲሆን ህትመቱም የያዛቸው ጠቃሚ ጥረቶችን ለሰፊው ታዳሚ ለማካፈል ያለመ ነው፡፡ ይህም አርሶ አደሮችን፣ ከፊል አርብቶ አደሮችን፣ አጋር አካላትን፣ ፖሊሲ አውጭዎችን፣ ተመራማሪዎችን እና የልማት ባለሙያዎችን ለማበረታታት እና በከፊል ደረቅ በሆኑ አካባቢዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማዳበር፣ ለመሞከር እና ለማላመድ ነው፡፡ ከፊል አርብቶ አደሮች በራሳቸው ልምዱን ሊካፈሉ ይችላል፡፡ የምርምር እና ልማት ድርጅቶችም መረጃውን በመጠቀም ለዘላቂ ልማት የሚረዱ የግብርና ልማት ስትራቴጂ እና ፖሊሲ ለመቅረፅ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

ታሪኩም በዋናነት የሚያውጠነጥነው የአካባቢው ህብረተሰብ በውስን በጀት ያስመዘገበው የፕሮጀክት ተግባራት ነው፡፡ ዳቦ ለዓለም (Bread for the world) የገንዘብ ድጋፍ በፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርቲየም በኩል "የሥነ ምህዳራዊ ግብርና አማካኝነት ማስፋፋት" በሚባለው ፕሮጀክት ብዙ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ ምርጥ ተሞክሮ ማህበር የስኬታማ ስራ መለኪያ የበጀት መጠን ሳይሆን ወደ አካባቢው ማህበረሰብ የሚያደርስበት አካሄድ ነው ብሎ ያምናል፡፡

የዚህ ህትመት ጥንቅር እና ህትመት ሊሳካ የቻለው በ"ዳቦ ለዓለም" (Bread for the world) ለጋሽ ቀና ድጋፍ በማድረጉ ነው፡፡

አስራት መንገሻ
የፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርቲየም የቦርድ ሊቀመንበር
አዲስ አበባ; ኢትዮጵያ
ጥቅምት 2013

# 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በተለያዩ የስነ ምህዳር አካባቢዎች የተከፋፈለች ሰፊ ሃገር ነች፡፡ ይህም የተለያየ ባህል እና የኢኮኖሚ ስርዓት ባለቤት እንድትሆን አስችሏታል፡፡ የአፋር ክልል በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ሰፋፊ ክልሎች አንዱ ሲሆን በውስጡም ብዙ የቤት እንስሳት እና ሰፋፊ የግጦሽ መሬቶች ይገኙበታል፡፡ ይሁንና አከባቢው ውሃ አጠር እና በተደጋጋሚ ድርቅ የሚጠቃ ስነምህዳር ያለው በመሆኑ የህብረተሰቡ ኑሮ ለችግር የተጋለጠ አድርጎታል፡፡ እንዲህም በመሆኑ በአብዛኛው ግዜ የአፋር ህዝብ ከከብት አርቢነት ውጪ በሌላ የልማት መስክ ላይ ሊሰማራ ይችላል ተብሎ አይታሰብም፤ አይገምትምም ነበር፡፡ እንደውም አፋር ውስጥ ከተረጅነት ውጪ ሌላ እንደጥምር ግብርና የመሳሰሉ የግብርና ስራዎችን ለመሞከርና ለመተግበር ማሰብ እንደእብደት የሚቆጥሩ ሰዎች እና አካላት ጥቂት አልነበሩም፡፡

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህን መሰሉን ግምታዊ እሳቤአቸው የተሳሳተ መሆኑን በተግባር ማሳየትና ማረጋገጥ የሚችሉ ታታሪ የአፋር ከፊል አርብቶአደሮች መከሰት ጀምረዋል፡፡ እንዲያውም ከዚያም አልፈው ለሌላው ማሳያና ማስተማርያ የሚሆኑ ስራዎችን የሚተገብሩ ሰዎች እንዳሉ ማየት ተችሏል፤ ይቻላልም፡፡ ከነዚህም መካከል በኮነባ ወረዳ የሚገኙ የማህበረተሰብ ክፍሎች ለዚህ ዋንኛ አብነቶች ናቸው፡፡

ኮነባ ወረዳ በሰሜናዊ አፋር ክልል ከዳሎል ዝቅተኛ ቦታ ኩታ ገጠም ላይ የሚገኝ፣ በጣም ሞቃትና ደረቅ የሆነ የአየር ፀባይ ያለው አከባቢ ነው፡፡ የዚህ ወረዳ ዋንኛ የውሃ ሃብት ደጋማዎቹ የጎረቤት የትግራይ አከባቢዎች ላይ ዝናብ ሲጥል ከሚወርደው ጎርፍ የሚገኘውን ሲሆን አልፎአልፎ ደግሞ

እጅግ አነስተኛ የሆነና የተቆራረጠ ቀላል ዝናብ ያገኛል፡፡ የዝናብ ስርአቱ የተዛባ በሚሆንበት ግዜም ባልተጠበቀ ደራሽ ጎርፍ ይጠቃል፡፡ ጎርፉም ሰው፣ ንብረትና እንስሳትን ጠራርጎ ስለሚሄድ የሚያደርሰው ጉዳት እጅግ የከፋ ነው፡፡ በእርግጥ በጎርፍ መልክ የሚወርደው ውሃ በተወሰነ ደረጃ ህብረተሰቡን የሚጠቅምበት አጋጣሚ ቢኖርም በአመዛኙ ሲታይ ግን የሚያደርሰው ጉዳት የዚያኑ ያህል ከባድ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ህዝቡ ዘወትር በአደጋ ተጋላጭነት ስሜት እና ድባብ ውስጥ የሚኖር በመሆኑ ከስጋት ተላቅቆ አያውቅም፡፡

ፔለም ኢትዮጵያ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ከሚገኙት አባል ድርጅቶቹ ውስጥ አንዱ ከሆነው ***የምርጥ ተሞክሮ ማህበር*** ጋር በመተባበር እንዲሁም ከወረዳው መስተዳድርና አርብቶ እና ከፊል አርብቶአደር ፅ/ቤት ጋር በመሆን ከ***"ብሬድ ፎር ዘ ወርልድ"*** (በተዛማጅ ትርጉሙ ዳቦ/ምግብ ለአለም እንደማለት ነው) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በኮነባ ወረዳ ላይ ***ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ግብርና*** በተለይም ***የጥምር ግብርና ስራ*** በማከናወን ይገኛል፡፡ ስራውን ጀምሯል፡፡ የዚህ ሃሳብ አመንጪዎችም ደግሞ የኩታ ገጠም ወረዳ (አፅቢ ወንበርታ አስተዳዳሪ የነበሩት) አቶ ሃፍቶም ውሬታ፣ የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት የነበሩት ፕሮፌሰር ምትኩ ሃይለ እና በጊዜው የኮነባ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ መሐመድ ኢድሪስ (በቅፅል ስማቸው እንድዕሉ) ናቸው፡፡

# 2. አጀማመር

ፕሮጀክቱን ለማስተዋወቅ ዝግጅት ሲደረግ በእቅድ ተይዞ የነበረው በአንድ ቢበዛ ደግሞ በሁለት ቀበሌዎች ላይ ሙከራ ማድረግ ነበር፡፡ በሂደት ግን የወረዳው ካቢኔ ተሰብስቦ በመመካከር በሰባት ቀበሌዎች ላይ እንዲሆን የሚል የውሳኔ ሃሳብ አቀረበ፡፡ በእኛ (በፕሮጅክቱ አስተባባሪዎች) በኩል ሰፋ አድርጎ መጀመሩ ጥሩ እንዳልሆነ ብንነግራቸውም እነሱ ግን "ህዝባችን ጠንካራ ሰራተኛ ነው፤ መንገዱን የሚያሳየው ሰው ነው እንጂ የጠፋው፣ አንዴ ስራውን የሚያስጨብጠው ካገኘ እራሱ በራሱ ያስቀጥለዋል" አሉን፡፡ ይህን መሰሉ (ህዝባችን ጠንካራ ነው) የሚለውን አባባል ደግሞ እውነትነት ለማረጋገጥ የሚያስቸግር፣ በብዙ ቦታዎች ላይ እንደመግቢያ በር የሚጠቀሙበትና የተለመደ ስለሆነ በሙሉ ልብ አልተቀበልነውም ነበር፡፡ ይልቁንም በእኛ በኩል ኪሳራ ሊያጋጥመን እንደሚችል ያለንን ስጋት እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔያቸውን ለመቀበል እየዳዳን ሳለ "እኛው ራሳችን የጎደለውን እየሞላን እንቀጥላለን" በማለት ፅናታቸውን ሲያረጋግጡልን ግን ቁርጠኛ አቋም መያዛቸውን ለመገንዘብ ቻልን፡፡ የውሳኔ ሃሳባቸውን ተቀብለንም የፕሮጅክቱ ዕቅድ ወደ ማሻሻል ተሸጋገርን፡፡ ሃሳባቸው እውን ሆኖ ለማየትም ጓጓን፡፡ ይህ ጠንካራ የመነሳሳት መገለጫ ክስተት ደግሞ ለእኛ የቆራጥነት ምልክት ሆኖ እንዲታየን ያደረገ መልካም ገጠመኝ ነበር፤ ብሩህ ተስፋ እንድንሰንቅም ያስቻለን ነበር ፡፡

ግንቦት 30 ቀን 2010 ዓ.ም ከእያንዳንዱ ቀበሌ አምስት-አምስት ሰዎች በተገኙበት የፕሮጀክቱ ትውውቅ ሰነስርዓት ተከናወነ፡፡ በጣም የሚያስገርመው በትውውቁ ወቅት አንዲትም ሴት አለመገኘቷ ነው፡፡ ባህሉ የማይፈቅድ ከመሆኑ የተነሳ እንደሆነ መገመቱ አያስቸግርም፡፡ ከዕድሜ ስብጥር አንፃር ሲታይም ጥቂቶቹ ወጣት ወንዶች ሲሆኑ አብዛኞቹ

ጎልማሳ አባወራዎች ነበሩ፡፡ በዕለቱ የተሳተፉት ዕድምተኞች አንዳንዶቹ ስራው ላይ ቀጥታ የሚሳተፉት ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ወላጆቻቸውን በተለይ እናቶቻቸውን በመወከል የተገኙ ናቸው፡፡

በወቅቱ የረመዳን ፆም ስለነበረ ስብሰባ መጥራት እና መሰብሰብ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚያ በጠራራ ፀሃይና ሙቀት ላይ ፆም ሲታከልበት ስብሰባ ማካሄድና በንቃት ማሳተፍ እጅግ ፈታኝ ስለሚደርገው ነው፡፡ በትውውቁ ወቅት በፆሙ ምክንያት የሻይ፣ ቡና፣ ውሃ፣ ወተት መስተንግዶ ወይም በተለምዶ የሻይ እረፍት የሚሉት ነገር አልነበረም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን አጠር እድርጎ መቋጨት እንጂ ማንዛዛት አላስፈለገም፡፡ ለነገሩ ከአፋሮች ጋር ሲወያዩ መንዛዛት ብሎ ነገር የለም፡፡ በአፋር የቀጠሮ ሰዓት ማዛነፍ አይታሰብም፡፡ ይልቁንስ ወሳኙ ጉዳይ የአፋሮቹ ሳይሆን ቀጠሮ ሰጪው አካል አርፋጅ ነው ወይስ በሰዓቱ ይመጣል የሚለው ነው፡፡ ማለትም ቀጠሮ ሰጪው አርፋጅ ከሆነ ያረፍዳሉ በሰዓቱ የሚመጣ ከሆነ ደግሞ እነሱም በሰዓታቸው ይገኛሉ፡፡

እኛ የፕሮጅከቱ አስተባባሪዎች ከመቀሌ ተነስተን ኮነባ ስንደርስ አብዛኛዎቹ ተሰብሳቢዎች በቦታው የተገኙ ሲሆን ራቅ ካሉ ቀበሌዎች (እንደ በልበል፣ ፊሾ፣ ወዘተ) ተሳታፊዎች ደግሞ ጥቂት ዘግየት ብለው ስለደረሱና ሁሉም ተሳታፊ ስለተገኘ ስብሰባው በወረዳው አስተዳደር ፅ/ቤት በሚገኝ በአነስተኛዋ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ተጀመረ፡፡

የወረዳው አስተዳዳሪ የነበረው አቶ መሐመድ ጭምትና ወጣት ቢሆንም በሁሉም የእድሜ ክልል የሚከበር ሰው ስለሆነ በሁሉም ዘንድ ላቅ ያለ ተደማጭነት አለው፡፡ ለነገሩ የአፋር ሰው ሁሉንም ሰው በእኩል ይሰማል፣ ይሰማል/ ያዳምጣል፡፡ ስብሰባው በአፋርኛ በመሆኑ ጥቂት በጥቂት ይተረጉሙልን ነበር፡፡ ከመድረኩም ለተሳታፊዎች ገለፃ

ሲደረግ ልማት እንደሚያስፈልግ፣ ተመርጠው የመጡትም ፕሮጀክቱ ለአከባቢው ማሕበረሰብ ያቀዳቸውን የልማት ዕቅዶች ያስፈፅማሉ ተብለው ታምኖባቸው እንደሆነ እና ህብረተሰቡን ወክለው የልማት ሃላፊነት ወስደው እንዲተገብሩ መሆኑን ገለፃ ተደረገላቸው፡፡ ተሳታፊዎችም በዚያው ልክ ሃሳቡን ሰምተዉትና ደግፈዉት እንደመጡ ምላሻቸውን ሰጡ፡፡

በስተመጨረሻ በሁላችንም ዘንድ አግራሞትን የጫረ አስተያየት የታከለበት ጥያቄ ከተሳታፊዎች ተሰነዘረ፡፡ እኛም እጅግ ነበር የገረመን፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት "እኛ በልማት የሚመራን በማግኘታችን ደስ ብሎናል፤ ምክንያቱም ሌላ ቦታ አትክልት እና ፍራፍሬ ሲያመርቱ በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን ስንሰማና ስናይ እንቀና ነበር፤ እነሱ እንዴት አድርገው እንደሚሰሩት ማየት እና መማር እንፈልጋለን፡፡ ሁላችንም እንደተነገረን አድርገን ቆፍረን፣ ጉድጓዱን ፍግ ከአፈር አደባልቀን ሞልተን፣ ቀጥሎም ውሃ አጠጥተን ነው የመጣነው" አሉ፡፡ እንዴት እንደቆፈሩት ሲጠየቁም ባለሙያ በነገራቸው መሰረት አንድ ክንድ (ግማሽ ሜትር) ጥልቀት በአንድ ክንድ (ግማሽ ሜትር) ስፋት እንዳዘጋጁ በዝርዝር አስረዱን፡፡

በመቀጠልም “እንዳትረሱ! ችግኙን እንዴት እንደምንተክል አንድ በአንድ አሳዩን፤ ከዚያም ችግኙን አከፋፍሉን፤ ከየአካባቢው አምስት አምስት ሰው ሆነን በመምጣታችን አንዱ ቢረሳ ሌላው ስለሚያስታውስ የሚረሳ ነገር አይኖርም፤ ስንተክልም አንሳሳትም፡፡” በማለት አረጋገጡልን፡፡ ይህን ሲሉ መድረኩን ስንመራ የነበርነው የፕሮጀክቱ ሃላፊና አስተባባሪዎች ባንድ በኩል የአድናቆት በሌላ በኩል ደግሞ ሃፍረት የተቀላቀለበት ስሜት ነበር የተሰማን፤ ምክንያቱም በዚህ ሰዓት የፕሮጀክት ትውውቅ እንጂ የችግኝ ማከፋፈል ፕሮግራም ባለመሆኑ እና ባለማዘጋጀታችን ነበር፡፡

በጣም ነበር የተከፉት፡፡ "በፆም ምድር የቆፈርነው እኮ ችግኝ ይመጣል ስለተባልን ነው" በማለት ቅሬታቸውን ገለፁልን፡፡ "ለማንኛውም ሳንተዋወቅ እና ምን እንደምትፈልጉ ሳንጠይቅ ችግኝ ገዝቶ ማምጣቱ አስፈላጊ ብለን ስላልገመትን ነው፡፡" ስንላቸው ደስ ባይላቸውም ተስማሙ፡፡ በመጨረሻም የፈለጉት ችግኝ በቅርብ ጊዜ እንደሚመጣላቸው በመግባባት ተለያየን፡፡

## 2.1. የፕሮጀክት ተጠሪ ሆኖ መመደብ

በስብሰባው ማለቂያ የወረዳው አስተዳዳሪ ለዚህ ፕሮጀክት ትግበራ የሚሆን አገናኝ ሰው አቶ ኑሩሑሴን ከማልን በመምረጥ መድቦ ሰጠን፡፡ ኑሩሑሴን በጣም ታታሪ ሰራተኛ ብቻ ሳይሆን ቀና ሰውም ነው፡፡ ከፊል አርብቶ አደሮቹ ኑሩሁሴንን ያምኑታል እንዲሁም በጣም ይወዱታል፡፡ አቶ ኑሩሁሴን የከፊል አርብቶ አደሮቹን ባህሪይ እና ባህል በጣም ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ስለፕሮጀክቱ እሱ ከነገራቸው ትክክለኛ መሆኑን አምነው ይቀበላሉ፡፡ በመሆኑም የአቶ ኑሩሑሴን ተጠሪ ሆኖ መመደብ ሁሉንም ወገን ያስማማ ነበረ፡፡



ምስል 1፡ ኑርሁሴን እና ከፊል አርብቶአደሮች የመስክ ምልከታ

## 2.2. አዲስ ሃሳብ

ቀጣይ ስልጠና እናካሂዳለን የሚል ፕሮግራም በፕሮጀክቱ ቢኖረንም አርሶአደርን፤ አርብቶ አደርን እና ከፊል አርብቶአደርን በስብስባ አዳራሽ ውስጥ እየሰበሰቡ ስልጠና መስጠቱ የሚፈለገውን ያህል ውጤት የሚያስገኝና ተመራጭ ስልት ተደርጎ አይወሰድም፡፡ በአዳራሽ ውስጥ የሚደረግ ስልጠና አበል ከመውሰድ ባለፈ ፋይዳው እምብዛም ነው፤ ሌላው ችግር በአቅራቢያው ያለ ሰው ጭምር እየመጣ በመቀላቀል የክፍያ አተካራ በመፍጠር ጨዋታው በአበል እና በክፍያ ላይ እንዲያተኩር ስለሚያደርገው የስልጠናውን አላማ በማሳት ከታለመለት ግብ እንዳይደርስ እንቅፋት ይሆናል፤ ስልጠናውንም በስተመጨረሻ ከዓላማው ውጪ ያደርገዋል፡፡ ቀጣዩን የፕሮጀክት ዓላማም በተመሳሳይ ለእንዲህ መሰል የአበል እና ጥቅማጥቅም ትኩረት የመጋለጥ ዕድሉ ሰፊ ስለሆነ ከአዳራሽ ውስጥ ስብሰባ ይልቅ የመስክ ጉብኝት የበለጠ ያሳምናቸዋል የሚል እምነት እና ስምምነት ላይ ደረስን፡፡

ከዚህም የተነሳ ከአከባቢው ማህበረሰብ መካከል ታታሪ ተብለው የሚገመቱ፣ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ስራ የጀመሩና በተጠቃሚ አባላቱ ዘንድ ላቅ ያለ አመኔታ ያላቸው ሰዎች ተመርጠው፣ በሌሎች አከባቢዎች የሚገኙ የመልካም ተሞክሮ ስራዎችን በአካል ተገኝተው በአይናቸው ቢያዩ የተሻለ እና የስራ መንፈሳዊ ቅናት እንደሚፈጥርላቸው ሃሳብ ቀረበ፡፡ ይህም አካሄድ ተቀባይነት አገኘ፡፡ የላቀ ፋይዳ እንደሚያስገኝም ታመነበት፡፡ ሌላው የአከባቢው ህብረተሰብ ደግሞ እነዚህ ሰዎች ከሚያመጡት ተሞክሮ እና ሃሳብ እየተካፈለ ይማራል፤ ያምናልም፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑት ሰዎች ያዩትን በተግባር ማሳየት ሲጀመሩ ህብረተሰቡን ማሳመን ቀላል ያደርገዋልና ነው፡፡

ከዚህም በመቀጠል ወዴት ቢሄዱ የተሻለ ተሞክሮና እውቀት ይዘው ይመጣሉ የሚለው ደግሞ ወሳኝ ጥያቄ ነበር፡፡ ብዙ ለጉብኝት የሚሆን በርከት ያለ የቦታ ዝርዝር በመምጣቱ የሚጎበኙትን ቦታዎች ለመለየት የተወሰኑ መመዘኛዎች ማውጣት ግድ ይል ነበር፤ አወጣንም፡፡ ከነዚህም መመዘኛዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፡-

- **አንደኛ፡-** ለማየት የሚመረጠው ውጤታማ ስራ በተለይ ምርጥ ተሞክሮ ሲያዩት የሚስብ እንዲሁም ለጎብኚ የሚያስቀና መሆን አለበት፡፡
- **ሁለተኛ፡-** የሚታየው ውጤታማ ስራ ወይም ምርጥ ተሞክሮ በግል ገበሬ የተሰራ እንጂ በድርጅት መሆን የለበትም፤ ምክንያቱም በድርጅት የተሰራ ከሆነ ጎብኝዎች "በግለሰብ ደረጃ ሊሰራ አይችልም"የሚል እሳቤ ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚለውን ስጋት ስለሚያቃልል ነው፡፡
- **ሶስተኛ፡-** የሚጎበኘው ቦታ ፀሃያማ እና ዝናብ አጠር መሆን አለበት ምክንያቱም ከጎብኚው ወረዳ (ከኮነባ) የአየር ፀባይ ጋር ተመሳሳይ አለያም ተቀራራቢ መሆን ይኖርበታል፤ ዝናብ ባይኖር እንኳን እንደዚህ ዓይነት ስራ መሰራት እንደሚቻል ማሳያ ይሆናል፡፡ ለጎብኚዎቹም በጣም ሳቢ እና አሳማኝነቱም የላቀ ይሆናል፡፡
- **አራተኛ፡-** የሚታየው ምርጥ ተሞክሮ ለውጡ ሳቢ ቢሆንም አካባቢው ግን የተጎዳ (የተጎሳቆለ) እና እንዴት ሊለወጥ ቻለ ብለው የሚገረሙበት መሆን አለበት፡፡
- **አምስተኛ፡-** ባለቤቱ አንድ ቤተሰብ በተለይ ሴት (እማወራ) የምታንቀሳቅሰው ቢሆን ይመረጣል፡፡

ምክንያቱም ጎብኘው እሷ እንደዚህ መስራት ከቻለች እኔስ ምን ይገደኛል? ለምን አልሰራም? ከማለት አልፎ የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊነትን ይገነዘቡበታል፡፡

ብለን ከተወያየን በኋላ በመመዘኛዎቹ መሰረት ሁለት ቦታዎችን ለየን፡፡ እነዚህ ቦታዎችም ቆላ ተንቤን ወረዳ የሚገኘውን የአቶ ወልደገብርኤል ድምፁ ስራ እና መረብ ለኽ ወረዳ የሚገኘው የወ/ሮ ሃረጉ ኀበዛይን የልማት ስራ ለመመረጥ ቻሉ፡፡ ሁለቱም ወረዳዎች ቆላማ እና ዝናብ አጠር ከመሆናቸውም ባሻገር የባለቤቶቹ ጥረት በመመዘኛዎቹ መሰረት ተገቢነታቸውንና ማራኪነታቸውን ስለታመነበት ነው፡፡

## 2.3. የትምህርታዊ ጉዞ ቅድመ ዝግጅት

ጊዜው የፆም ወቅት (በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በልዩ ሁኔታ የሚከናወን) ስለነበር ትምህርታዊ ጉብኝቱን ከፆም በኋላ ከሰኔ 14-17 2010 ዓ.ም (ከ22-25 ጁን 2018) ባሉት አራት ቀናት ለማካሄድ ዕቅድ አወጣን፡፡ ከሰባቱ ቀበሌዎች አምስት - አምስት ከፊል አርሶአደሮች ማሳተፍ የካፒታል ዓቅማችን ስለሚገድበን ለመጀመሪያው ትምህርታዊ የጉብኝት ጉዞ ግማሹን ብቻ ለማሳተፍ ዝግጅታችንን አጠናቀቅን፡፡ በዝግጅቱ ላይ ሴቶች ለማካተት ግፊት ብናደርግም ከአካባቢው ባህል አንፃር ሊሳካልን አልቻለም፡፡ ያም ሆኖ ግን አርአያ የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉ እንዳሉ ለመገንነዘብ አላዳገተንም፡፡ ለምሳሌ ወ/ሮ አስያ ከበልበል፣ ሃዋ ኢብራሂም ደናን ከዒንደሊ፣ ወ/ሮ መርየም ከኮነባ ከተማ፤ ወዘተ፡፡ ስለዚህ የሴቶችን የማሳተፍ እቅድ አንድ ወቅት ላይ ሊሳካ ይችላል በሚል እሳቤ በይደር እንዲቆይ ተደረገ፡፡ ምክንያቱም ከባህል እና ልማድ ጋር መጋፋት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናልና ነው፡፡



ምስል 2፡- በበረሃው መሃል እድሜ ጠገብ ሎሚ

በዚህ መሰረት ሰኔ 14 ቀን 2010 ዓ.ም 21 ተሳታፊዎች (18 ከፊል አርብቶአደሮች እና 3 ባለሙያዎች) ይዘን ወደ ትምህርታዊ ጉብኝቱ ተንቀሳቀስን፡፡ ከጉብኝቱ በፊት በመቐለ ከተማ የሻይ ሰአት ወቅት መጠነኛ ውይይት አደረግን፡፡ ዶ/ር ሃይሉ አርአያ የጉብኝቱን ዓላማ ድጋሚ በይበልጥ ካብራሩላቸው በኋላ ተሳታፊዎቹ በዓይን ማየቱ ተቀባይነት ያለው ትክክለኛ ሃሳብ እንደሆነ በድጋሚ አረጋገጡልን፡፡ ሼክ ሑሴን መሐመድ የተባሉ ተሳታፊ ስለጠቀሜታው ከሰጡት ምላሽ ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፡- *"ጀሮ እና ምላስ በኮነባ በሙሉ፣ በአፋር ክልል በሙሉ፣ በኢትዮጵያ በሙሉ አለ፡፡ በጣም ብዙ ነው፡፡ አንዳንዱ የሰማውን ያወራል፣ ሌላው ደግሞ ያየውን ያወራል፡፡ ለሰሚው ሃቁ የትኛው ነው? ብሎ መለየት ግን በጣም ይከብዳል፡፡ ምክንያቱም ለሰሚው ሁለቱም ወሬ ናቸው፡፡ እራስህ ያየኸው ከሆነ ግን ከሁሉም በላይ ታምነዋለህ፡፡ አላህ በሰጠህ አእምሮ የገባህ ደግሞ ወስደህ ትተገብረዋለህ፡፡ አሁንም እኔ ልማቱ በአይኔ ካየሁ በኋላ ነው መናገር የምፈልገው"* በማለት ነበር ያብራሩት፡፡ ሌሎችም ሃሳብ ለመስጠት ቃል ገብተው የነበረ ቢሆንም፤

በስተመጨረሻ ዝምታ መምረጣቸው ‘መናገር የምንሻው ካየን በኋላ ነው‘ የሚል አንደምታ ነበረው፡፡



ምስል 3፡- በኮነባ ከተማ የሚገኘው የወ/ሮ መርየም ግቢ

# 3. የመጀመሪያው የትምህርት ጉብኝት

## 3.1. የአርሶአደር ወ/ገብርኤል የልማት ክንውኖች ጉብኝት

አንደኛው የትምህርታዊ ጉዞ ጉብኝት ወደ ቆላ ተንቤን የትግራይ ማእከላዊ ዞን ነበር፡፡ የአርሶአደር ወልደገብርኤል ድምፁ ቤት የሚገኘው ከአብይ ዓዲ ከተማ ወጣ ብሎ ሲሆን ቦታውም ሞቃታማ እና ደረቃማ ብቻ ሳይሆን አፈር አልባም ጭምር ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ የተሰጠው መሬት ለእርሻ የሚሆን አልነበረም፡፡ ዋናውንና የማሳውን ሰፋ ያለው ክፍል ኮረብታማ ስፍራ ላይ ያረፈ ከመሆኑም ባሻገር ታችኛው ክፍሉም ሰፊ ቦረቦር ያለው ነበር፡፡ እዚህ ኣካባቢ መጠነኛ ዝናብ ሳይቀር ጎርፍ ስለሚያስከትል እግረኛ/ መንገደኛ በዚያው በኩል መሻገር አይችልም፡፡




*ምስል 4፡ የአርሶአደር ወ/ገብርኤል ቦታ ገፅታ*

አርሶአደር ወልደገብርኤል የግንበኛነት ልምድ ስላለው ይሄን ችሎታውን ተጠቅሞ አካባቢውን መለወጥ እንደቻለ ማሳያ የሚሆኑ ስራዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

- **አንደኛ፡-** በኮረብታማው መሬት ከአንድ ሜትር በላይ ከፍታ ያላቸውን እርከኖች በመስራትና ለቋሚ አትክልት መትከያ የሚሆን ደልዳላ ቦታ በማዘጋጀት የተለያዩ አትክልቶች መትከል ችሏል፡፡ ለአብነትም ከተከለው ቋሚ የማንጎ ዛፍ ስር ሌሎች ጊዚያዊ አትክልትንም አብሮ ያለማል፡፡

- **ሁለተኛ፡-** የአርሶአደር ወልደገብርኤል መሬት በተፈጥሮው ደልዳላ መሬት ባይኖረውም የጉብታው ዝቅኛውን ክፍል በመቆፈር ከጉብታው ስር አካባቢ የተወሰነ ደልዳላ መሬት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በዚህም ቦታ ላይ በጥቂቱ፡-

  1. የተለያዩ ቋሚ ተክሎች እንደ ማንጎ፣ ብርትኳን፣ ወዘተ ተክሏል፣
  2. ወቅታዊ (በአጭር ጊዜ የሚደርሱ) አትክልቶችን እንደ ጎመን የመሳሰሉትን ተክሏል፣
  3. ባልተለመደ ቦታ ስንዴ ዘርቶ ጥሩ ምርት አግኝቷል
  4. ለከብት መኖ የሚሆን እንደ አልፋአልፋ ዘርቷል፣
  5. የውሃ ማቆርያ እና የውሃ ማጠራቀሚያ ሰርቷል፣ እንዲሁም
  6. የኮምፖስት ማዘጋጃ ሰርቷል፡፡

- **ሶስተኛ፡-** ከጉብታው ስር ያለው ቦረቦር ትልቅ ቢሆንም እላዩ ላይ የአፈር ባንክ እና የውሃ ማቆርያ ቼክ ዳም ሰርቷል፡፡

- **አራተኛ፡-** በተዳፋቱ ላይ ለንብ ማነብያ የሚሆን ቦታ በማመቻቸት የንብ ቀፎዎችን አስቀምጧል፡፡

- **አምስተኛ፡-** የውሃ ችግሩን ለማቃለል በተዳፋቱ ቦታ ላይ ስፋቱ 6 ሜትር በ6 ሜትር፣ ጥልቀቱ 3 ሜትር የሆነ የውሃ ማጠራቀሚያ በጋብዮን፣ ሲሚንቶና ፌሮ ገንብቶ የውሃ አማራጭ እንዲኖረው አስችሎታል።
- **ስድስተኛ፡-** ጉብታው ጫፍ አካባቢ አነስ ያለች ቦታ በመደልደል የዶሮ እና የወተት ከብት እርባታ፣ መኖርያ ቤት እንዲሁም የባዮጋዝ ማብላያ በመገንባት የታዳሽ ሃይል ተጠቃሚ ለመሆንና ተጨማሪ ገቢ በማመንጨት ኑሮውን ለማሻሻል ጥረት አድርጓል።

በአጠቃላይ ሲታይ የአርሶአደር ወልደገብርኤል ቦታ ከአካባቢው የተለየ ልምላሜ ያለው አረንጓዴ ለብሶ ሲታይ አይን የሚስብ የእምነት ቦታ ይመስላል። ጎብኝዎቹ ምንም እንኳን ከፊል አርብቶአደር ቢሆኑም የአካባቢው አየር ንብረትና የመሬቱ ሁኔታ ከነሱ አካባቢ ጋር እንደሚመሳሰል በማየታቸውና ኮነባም እንደዚህ የመሆን ተስፋዋ ሲፈነጥቅ ሳይታያቸው አልቀርም፤ አጅጉን ነበር የተደሰቱት።




ምስል 5፡ የወልደገብርኤል የልማት ስራዎች በከፊል (ለቁጥሮቹ መግለጫ በምስል 4 ላይ ይመልከቱ)

## 3.2. የወ/ሮ ሃረጉ እርሻ ስራ ጉብኝት

ወ/ሮ ሃረጉ ኀበዛይ የመረብ ለኸ ነዋሪ ናቸው፡፡ መረብ ለኸ ወረዳ በሰሜን በኩል ትግራይ ክልልን ከኤርትራ የሚያዋስን ወረዳ ነው፡፡ ሞቃታማ እና ዝናብ አጠር ኣካባቢ ሲሆን፣ መሬቱ ወጣ ገባ እንዲሁም ከተወሰኑ የደለል መሬቶች ውጪ ጭንጫማ ነው፡፡

የወ/ሮ ሃረጉ መሬት ከመጀመሪያው ጭንጫማ፣ ጨዋማ፣ እንዲሁም በአቀንጭራ አረም የተወረረ ስለነበረ እንደማይጠቅም የተቆጠረ መሀን መሬት ተብሎ ለከብት መዋያነት የተተወ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ግን ዳጉሳ፣ ማሽላ እንዲሁም ጤፍ ያበቅል ነበር፡፡ ወ/ሮ ሃረጉ ግን ሰው ከለፋ እና ከሰራ መሬት የተባለ ሁሉ ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችል አሳይተውናል፡፡

ግለ ታሪኳን ለትምህርታዊ ጎብኝዎች እንደነገረቻቸው ከሆነ የዛሬ 12-14 ዓመት አካባቢ ባዶ መሬት ነበር፡፡ ሞተር ተከራይታ ትንሽ መስኖ በመጠቀም አትክልት ማምረት እንደጀመረች እና ጎን ለጎን ደግሞ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ መንደሪን እና በርቱኳን መትከል እንደጀመረች ትናገራለች፡፡



ምስል 6፡ በጊዜያዊ ፓፓያ የተሸፈነ የወ/ሮ ሃረጉ የአፈር ባንክ በከፊል

አሁን ግን የእሷ የእርሻ መሬት የበረሃ ገነት ይመስላል፡፡ አሁን ያላት የመሬት ስፋት 12 ሄክታር ሲሆን ይዞታው

ደግሞ በከፊል የራሷ፣ በኪራይ እና በልዋጭ አማካይነት የተያዘ ነው። እዚሁ የእሷ ይዞታ ውስጥ

- ዶሮ እርባታ በአንድ በኩል፣
- የወተት ከብቶች እርባታ በሌላ በኩል፣
- ባዮጋዝ ማብለያ እዚያው፣
- ከ50 በላይ የኮምፖስት ጉድጓድ፣
- ስድስት አንድ ሜትር ስፋት፣ አንድ ሜትር ጥልቀት እና ሶስት ሜትር ርዝመት ያላቸው የቨርሚ ኮምፖስት ጉድጓዶች፣
- አንድ የአፈር ባንክ፣
- ከ10 000 በላይ የማንጎ ችግኝ፣ ወዘተ ይገኛሉ።



ምስል 7፡ የወ/ሮ ሃረጉ ጎበዛይ ችግኝ እና የእርሻ ውጤት በከፊል

ወ/ሮ ሃረጉ ለቋሚ ተክል ችግኝ መትከያ የሚሆነውን ጉድጓድ ካስቆፈረች በኋላ የሚሞላውን ፍግ ወይም ለም አፈር ከሩቅ ቦታ በየቀኑ በግመል በማመላለስ ነበር የምትጠቀመው። የዛሬ 6-7 ዓመት ግን የውሃ ባንክ ሲባል ብትሰማም የሷ ዋናው ችግር አፈር ስለሆነ ለምን የአፈር ባንክ አልሞክርም አለች። ለዚህ ደግሞ ጥሩ መፍትሄ የሚሆነው በአካባቢዋ ያለው

ወንዝ ሞልቶ ጎርፍ በሚሆንበት ግዜ መሆኑን ተገነዘበች፡፡ ወንዝ ላይ ወርዳ ስትመለከተው/ ስትታዘበው ደግሞ ጎርፉ ሲወርድ ይዞት የመጣውን አለት፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ እንዲሁም ለም አፈር የሚጥልበት ቦታ የተለያየ መሆኑን ተገነዘበች፡፡ ስለዚህ ከእርሻዋ ጎን ያለው ወንዝ ጎርፍ በሚሆንብት ግዜ ጎርፉ በርሷ እርሻ ተቃራኒ የወንዙን ግድግዳ በመምታት ሲመለስ በመጀመሪያ ቀጥታ የሚጥለው ጠጠር ሲሆን ቀጥሎ ለም አፈር ይጥላል ስለዚህ የመጣው ለም አፈር የሚያርፍበት ቦታ ከቅርቧ በድንጋይ አጥር በመከለል የአፈር ባንክ ፈጥራለች፡፡

ከሁለት አመት በኂላ የምትፈልገውን ያህል አፈር ሰበሰበች፡፡ እንዲያውም እዚያ ቦታ ላይ የተከማቸው አፈር ከሚያስፈልጋት በላይ በመሆኑ ከአፈር ባንክነት አልፎ ጊዚያዊ የፓፓያ መትከያ እንዲሆን አደረገችው ምክንያቱም የደለበ መሬት በመሆኑ ለም አፈር ሲያስፈልግ ለም አፈር እየሰጠ ጥቅም ላይ እንዲውል ተብሎ የታቀደበት ቦታ ነው፡፡




ምስል 8. የወ/ሮ ሃረጉ የእርሻ ቦታ ገፅታ

የወ/ሮ ሃረጉ ቤተሰብ ከእርሻው በተጨማሪ የወተት እና ዶሮ እርባታ አላቸው፡፡ የወተት እርባታው 8 የወተት ከብቶች ያሏቸው ሲሆን እነሱን ለመመገብ ተቸግረው አያውቁም፤ ወይም መኖ ለመግዛት ሌላ ተጨማሪ ወጪ አውጥተው አያወቁም፤ ምክንያቱም ሁሉም አቅርቦት በእርሻው ውስጥ ስላላቸው ነው፡፡ የወ/ሮ ሃረጉ እርሻ ራሱን የቻለ እና ከውጭ ምንም ነገር የማይፈልግ ሲሆን ከእርሻው ወደ ውጭ የሚሄደው ወተት እና ፍራፍሬ ብቻ ሲሆን በተጨማሪ ከእርሻው የከብት መኖ ይገኛል፡፡ የከብት መኖው ለወተት ከብቶች ይሰጣል፣ የወተት ከብቶች ደግሞ ወተት እና እበት ይሰጣሉ፣ የከብት እበት ወደ ባዮጋዝ ይሄዳል፣ ከባዮ ጋዝ ወደ ኮምፖስት ወይም ቀጥታ በማዳበርያ እጥረት የተጠቃ ቋሚ ተክል ካለ እሱ ላይ ይደረጋል፣ ከኮምፖስት ወደ ቋሚ አትክልት ይጨመራል፣ ወተቱ ደግሞ ለገበያ ይሄዳል፣ ወዘተ ነው፡፡ ስለዚህ ወጪ ሳይኖር በየቀኑ ቤተሰቡ ብዙ ገቢ ከወተት ይሰበስባል እንዲሁም ከወተቱም ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

አሁን የወ/ሮ ሃረጉ ቤተሰብ ሃብት ተቆጥሮ የሚያልቅ ሳይሆን በኢንቨስተር ደረጃ የሚታይ ነው፡፡ የወ/ሮ ሃረጉ ቤተሰብ ከምንም ተነስተው ከእርሻው ተጨማሪ አሁን ያላቸው ሃብት ሁለት ባለ ሁለት ደብር ፎቆች ተጠናቆ ስራ ላይ ሲሆን፣ አንድ ባለ ስድስት ደብር ፎቅ ደግሞ በመሰራት ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ሰአት የወ/ሮ ሃረጉ ቤተሰብ ሃብት በግምት ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ ነው፡፡

የጉብኝቱ ተሳታፊዎች ከተመለሱ በኋላ ከጉብኝቱ ተማርን ብለው የተናገሩት እንደሚከተለው ነበር፡፡

- አንደኛ፡- ራማ ከተማ ከደረሱ በኋላ የአየሩ ሁኔታ ከኮነባ ጋር ልዩነቱ ለማወዳደር ሲባል በእግራቸው እንዲንቀሳቀሱ ተደርጓል፡፡ የፀሃዩ ሙቀት ከባድ በመሆኑ ከነሱ አካባቢ የሚመሳሰል ቢሆንም የወ/ሮ

ሃረጓ እርሻ ላይ ሲገባ ግን ጫካ ውስጥ እንዳለህ ይሰማሃል፡፡ ስለዚህ የየራሳቸው መሬት እንዲህ ቀይረው መለወጥ እንደሚችሉ እና እንደሚፈልጉ ተናግሯል፡፡

- **ሁለተኛ፡-** ማንኛውም አካባቢ ሰው ከሰራ መለወጥ የሚችል መሆኑ በእርሻው ውስጥ ያሉ ምልክቶች በማየት አረጋግጠዋል፡፡ ይሄን ካዩ በኋላ የነሱ መሬት እንደሚበልጥ እና የተሻለ መስራት እንደሚችሉ ተናግሯል፡፡
- **ሶስተኛ፡-** ሴቶች ጠንካሮች መሆናቸው እናውቃለን ይሄን ያህል ስለመሆኑ ለማመን ቢከብድም በአይን ማየት ግን ከሁሉም በላይ አሳማኝ ነበር፡፡ አስገራሚው ደግሞ ወ/ሮ ሃረጉ ወንድ ያልሰራበት የእርሻ መሬት እየተከራየች መስራቷ ወንድን አስንቃለች፡፡
- **አራተኛ፡-** እኛ እጅ ያለው መሬታችን የምንፈልገው ወርቅ የሚሰጠን ከሆነ የሰው አገር ያለውን ወርቅ ፍለጋ ስደት ለምን ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እኛ ከሰራን ወርቁ እዚሁ እኛው ጋር ነው ያለው ብለዋል፡፡

## 3.3. የዓድሓ ቀበሌ የልማት ስራ ጉብኝት

ዓድሓ በቆላ ተንቤን ወረዳ ውስጥ የምትገኝ ቀበሌ ስትሆን ውሃ አጠር እና አሸዋማ መሬት ያላት ብትሆንም በአንፃሩ በብርትኳን ፍራፍሬ ምርቷና ችግኝ አቅርቦቷ ስትታይ ደግሞ እጅግ ታዋቂነትን ያተረፈች ቀበሌ ነች፡፡ የትምህርታዊ ጉዞው ተሳታፊዎች ከዚህ የቀሰሙት ተሞክሮ እንደሚከተለው ነው፡፡

- አፋሮች ዓድሓና ምርቷን አይተው እንዲህ አሉ "አላህ ሰውን የፈጠረው ከነብልሃቱ ስለሆነ የትም መኖር ይችላል፡፡ ይህ ቦታ አስቸጋሪ እና አሸዋማ ነው ብለን የምንንቀው ነው፡፡ እኛ ከዚህ የበለጠ መሬት ይዘን

እንዴት መለወጥ ያቅተናል ብለዋል፡፡ ይህ ቦታ በልበልን ይመስላል፡፡ በልበል እንዲህ ነች፡፡"




ምስል 9፡ የዓድሓ የቋሚ ተክል እርሻ ቦታ

- ቀጠሉ "የምናያቸው ሰፋፊ እርሻዎች የመንግስት ወይም የኢንቬስተር ይዞታ ይመስሉን ነበር፤ ለካ ትናንሾቹ የገበሬ እርሻዎች አንድ ላይ ተደምረው ነው አንድ ትልቅ እርሻ የመሰሉን! ይህም የሚያሳየን የሁላችን ስራ አንድ ላይ ሲታይ ውበት እንዳለው ነው፡፡"

- "ችግኝ ማፍላት የመንግስት ስራ እየመሰለን ነበር የተቸገርነው፡፡ ለካ ግለሰቦችም ስልጠና ካገኙ ይሰሩታል! የሚያስፈልገው ስልጠናና የተወሰኑ አስፈላጊ መሳርያዎች ብቻ ናቸው፡፡" በማለት ቀድሞ የነበራቸውን ግንዛቤ ግርድፍ እንደነበር እራሳቸውን በራሳቸው ለማረም በቅተዋል፡፡

- "አሁን ገባኝ አሉ" ሸህ ሑሴን መሓመድ፡፡

## 3.4. የችግኝ ፍላጎት እና ተከላ

ከልምድ እንደምናውቀውና ሌላ ቦታ ላይ እንዳየነው ከሆነ በችግኝ እደላ ወቅት፡- በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደው አንድም ከተቻለ ከምትፈልገው ቁጥር በላይ ችግኝ መጠየቅና ሲበላሽብህ መተካት፤ ወይም ችግር ሲያጋጥምህ የሚመስል ምክንያት ፈልገህ መናገር ብቻ ነው፡፡ አንዳንዱ ቦታ ላይ ደግሞ አጠጋግተህ ትተክልና አንዱ ሲጠፋ የፀደቀውን መከታተል ነው፡፡ አለበለዚያ ለዘመድ ወይ ለጎረቤት ትሰጠዋለህ፤ ገፋ ሲል ደግሞ ትሸጠዋለህ፡፡

በአንፃሩ እዚሁ ኮነባ ወረዳ ያለው ሁኔታ ደግሞ በአፋር ባህል እና ባህርይ መሰረት የተደረገ ስለሆነ በአብዛኛው ያገሪቱ ክፍል ከሚያጋጥመው ፍፁም የተለየ ነው፡፡ የሚጠይቁት የችግኝ መጠን የቆፈሩትን ጉድጓድ ያህል ብቻ ነው፤ ይህም ሆኖ የሚፈልጉት የችግኝ ዓይነት ግን ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዱ ስንት ትፈልጋለህ ተብሎ ሲጠየቅ፣ "እኔ ያለኝ ጉድጓድ ይሄን ያህል ነው፤ ስለዚህ ይሄን ያህል ብርቱኳን፣ ይሄን ያህል ማንጎ፣ ወዘተ..." በማለት በቆፈረው ጉድጓድ ልክ ነው የሚጠይቀው፡፡ ኋላ ጉድጓድ ቆፍሬ እተክላለሁ ወይም ቢጠፋ እተካበታለሁ ብሎ ነገር የለም፡፡ ከጉድጋዱ ቁጥር አንዲትም እላፊ አይጠይቁም፤ እላፊ መጠየቅ "ሓራም ነው አላህ አይወደውም" ይላሉ፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በፕሮጀክቱ የተከፋፈለውና በራሳቸው ከጉብኝቱ ያሰባሰቧቸው የችግኝ መጠን እንደሚከተለው ነው፡፡

*ሰንጠረዥ 1፡ የተከፋፈለው የችግኝ መጠን በአይነት (በፕሮጀክት እና በህብረተሰቡ በራሳቸው ተነሳሽነት የቀረበ)*

| ተ.ቁ | ዓ/ም | ማንጎ | ሎሚ | ፓፓያ | አቮካዶ | ሙዝ | ብርቱኳን | ቡና | ዘይቱን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2010 (ፕሮ) | 70 | 74 | 70 | 50 | 70 | - | - | - |
| 2 | 2010 (በተ) | 200 | - | 50 | - | - | 80 | 50 | - |
| 3 | 2011 (ፕሮ) | - | 200 | - | 150 | - | - | - | 200 |
| 4 | 2011 (በተ) | 50 | - | - | - | - | 60 | 30 | - |
| 5 | 2012 (ፕሮ) | - | 400 | 250 | 100 | 200 | - | - | 150 |

*ፍቺ፡- ፕሮ (ፕሮጀክት)፣ በተ (በራሳቸው ተነሳሽነት)። አገር በቀል ዛፍ፡- 3000 (2011)፣ 2360 (2012)፣ ለአፕር ችግር መፍትሄ እንዲሆን 200 የኮሽም ችግኝ (2012)፣ 200 የቆላ ቀርከሃ ችግኝ (2011)፣ 20 የአፕል ችግኝ (2012)፣ ቢጫ ቀለም ያለው የሱኳር ድንች 400 ቁርጥራጭ (2010)፣ 8 ጥቅል የሸንኮራ አገዳ (2010) ተከፋፍሏል።*

*ሰንጠረዥ 2፡ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ እና በሰመራ ዩኒቨረሲቲ የተደረገ የችግኝ አቅርቦት እገዛ*

| ተ.ቁ | ዓ.ም. | ተቋም | ማንጎ | ሎሚ | ፓፓያ | አቮካዶ | ብርቱኳን | ቡና | ዘይቱን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2010 | መዩ | - | - | 300 | - | - | - | - |
| 2 | 2011 | መዩ | 50 | 300 | 150 | 50 | 185 | 150 | 100 |
| 3 | 2012 | ሰዩ | 4250 | 250 | 250 | - | 550 | - | 250 |

*በተጨማሪም የሰመራ ዩኒቨርሲቲ 14 ኪሎ ግራም የተለያዩ የጓሮ አትክልት ዘር አበርክቷል።*

## 3.5. የመረጃ ልውውጥ

ከእያንዳንዱ ጉብኝት በኋላ የተገኘው አዲስ መረጃ ህብረተሰቡ ዘንድ ለማድረስ እዳው ገብስ ነበር። ምክንያቱም በአፋር "ዳጉ" በሚባል ባህላዊ የመረጃ መለዋወጫ ስልት መሰረት እያንዳንዱ በየፊናው ያጋጠመውን መረጃ ለሚመለከተው ሰው ማስተላለፍ ባህላዊ ግዴታ ተደርጎ የሚወሰድ ስለሆነ ነው። ለዚህም ማረጋገጫ የሆነ አጋጣሚ ያኤውኑ ለማስተዋል በቅተናል። የመጀመሪያው ዙር ጉብኝት እንደጠናቀቀ በቅፅበት

ስለጉብኝቱ እና ስለተጎበኙ ቦታዎች መረጃ በሁሉም ቀበሌዎችና የቀበሌዎቹ ነዋሪዎች በመላ (በሁሉም ሰው ዘንድ) ተሰራጭቶ መገኘቱ አግራሞትና አድናቆት ሳንቸረው የማናልፈው ክስተት ሆኖብን ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ በርካታ ሰዎች ችግኝ ፍለጋ ወደ ወረዳ መስተዳድር ፅ/ቤት ድረስ በመምጣት ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ፡፡

- የህዝቡ ጥያቄ - "እኛም ችግኝ እንፈልጋለን፡፡ እንደነሱ እኛም ቋሚ ተክል መትከል እንፈልጋለን" የሚል ነበር፡፡
- የወረዳ አስተዳደር መልስ - "ፕሮጀክቱ የሚሰጠው ትንሽ ነው፤ እነዚህም ቢሆን ለተመረጡ ጥቂት ታታሪ ከፊል አርብቶአደሮች ብቻ የሚከፋፈሉ ናቸው፡፡"
- የህዝቡ ጥያቄ - "እና ተስፋ የለውም?"
- የወረዳው አስተዳደር መልስ - "የለውም፡፡"
- የህዝቡ ጥያቄ-"ችግኙ የት ይገኛል? ዋጋው ስንት ነው? እንዴትስ ማግኘት እንችላለን?"
- የወረዳ አስተዳደር መልስ - "የሚገኘው መቀሌ፣ ቆላ ተንቤን፣ ውቅሮ እና ራማ ነው፡፡ ዋጋው 100 ብር አካባቢ ነው፡፡ ለማንኛውም ኑርሁሴንን ጠይቁ፡፡"
- ከኑርሁሴን ጋር የተደረገ ጥያቄ - "እኛም ችግኝ መትከል እንፈልጋለን፣ በራሳችን ብር እንዴት እናገኛለን?"
- የኑሩሁሴን መልስ - "ከፈለጋችሁ እኔ ገዝቼ በትራንስፖርት ላመጣላችሁ እችላለሁኝ፡፡"
- ህዝቡ - "ሁሉንም ወጪ እንሸፍናለን" ብለው በአንዳፍታ **አስር ሺህ ብር** በማዋጣት ለኑሩሁሴን አስረከቡ፡፡ ፕሮጀክቱ በበኩሉ ችግኙን ለማጓጓዝ የትራንስፖርት ወጪ ሸፈነላቸው፡፡

እንዲህ አይነት ጥያቄ ያልተለመደ ነው፡፡ በማናቸውም ፕሮጀክት ታሪክ ዘንድ ህብረተሰብ ያቀረብክለትን እንዲተክል ሲለመን እንጂ ለምኖ ችግኝ ሲገዛ የተለመደ ክስተት አይደለም፡፡

# 4. ሁለተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት

ሁለተኛው የትምህርት ጉብኝት የተደረገው በመጀመሪያው ትምህርታዊ ጉዞ ላይ ያልተሳተፉትን የፕሮጀክቱ አባላት፣ ከሌላ ቦታ ለምሳሌ ከአዲስ አበባ እና ከሰሙሮቢ ገላዕሎ ወረዳ ተሳታፊዎችን በመጨመር ነበር፡፡ በጉዞው ላይ እንደበፊቱ ከፕሮጀክት ተሳታፊዎች ውስጥ አንዳችም ሴት ተሳታፊ አልነበረችም፡፡ በመጀመርያው ዙር ትምህርታዊ ጉዞ ወቅት የተጎበኙት ቦታዎች በዚህ የትምህርታዊ ጉዞ ፕሮግራም ላይም ሙሉ በሙሉ ተጎብኝተዋል፡፡ ሆኖም ግን የሚከተሉት ቦታዎች እና ስራዎች ተጨምረውባቸዋል፡፡ እነሱም፡-

አንደኛ፡- በወ/ሮ ሀረጉ እርሻ ከኮምፖስት ጉድጓዶች እና የአፈር ባንክ በተጨማሪ መጠናቸው 1*1*3 ሜትር የሆኑ በብሎኬት እና በሲሚንቶ የተሰሩ ቨርሚ ኮምፖስትን በየወሩ ለማምረት የሚረዱ ሁለት የቨረሚ ኮምፖስት ማምረቻ ግንባታዎች፡፡



ምስል 10፡- የወ/ሮ ሃረጉ ቨርሚ ኮምፖስት ጉድጓድ

<u>ሁለተኛ፡-</u> በአርሶአደር ወልደገብርኤል የእርሻ ቦታ ደግሞ የፈሳሽ ማዳበሪያ አዘገጃጀት እንዴት እንደሆነ በተግባር ከተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎች፣ ሽንት፣ እበት፣ ውሃ፣ ወዘተ እንደሚዘጋጅ በተግባር ሰልጥነዋል፡፡ በቦታው ተገኝተውም ፈሳሽ ማዳበርያን በሶስት ደረጃ ማዘጋጀት እንደሚቻል በተመለከተ የተዘጋጀውን ስልጠና እራሳቸውም ተግባሩ ላይ ተሳታፊ እየሆኑ ተከታትለዉታል፡፡ እነሱም፡-

- 1ኛ፡- ለስላሳ አረንጓዴ ቅጠላ ቅጠሎች አንድ ላይ በመውቀጥ ከውሃ ጋር እየቀላቀሉ ማዘጋጀት፤
- 2ኛ፡- ለስላሳ አረንጓዴ ቅጠላ ቅጠሎች አንድ ላይ በማድረግ ከወቀጡ በኂላ ከእበት ጋር በማቀላቀል በውሃ በመቸለስ ማዘጋጀት፤
- 3ኛ፡- ለስላሳ አረንጓዴ ቅጠላ ቅጠሎች አንድ ላይ በመውቀጥ፣ ከእበት እና ከሽንት ጋር ማቀላቀል እና ከውሃ ጋር እያወሃዱ ማዘጋጀት የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የፈሳሽ ማዳበሪያ በሰብል እና በተለያዩ አትክልቶች ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ ምን እንደሚመስልና እንዴት እንደሚዘጋጅን በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው የጉብኝት ቦታ (በአርሶአደር ገብረየሱስ ቤት) ላይ እንደሚያዩ ቃል በተገባላቸው መሰረት ለስልጠና ወደ አክሱም አካባቢ ሄደዋል፡፡

<u>ሶስተኛ፡-</u> አርሶአደር ገብረየሱስ ተስፋይ በትግራይ ክልላዊ ብሄራዊ መንግስት፣ ማእከላዊ ዞን፣ ታህታይ ማይጨው ወረዳ፣ የከዋኒት ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ ከዋኒት ቀበሌ በአክሱም ከተማ አቅራቢያ ትገኛለች፡፡ አርሶአደር ገብረየሱስ በተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ እና የተፈጥሮ የፀረ

ተባይ ዝግጅት እና መከላከል ረገድ አድናቆት ያተረፉ የአርሶአደር ዶክትር ያስባ ታዋቂ አርሶአደር ናቸው፡፡ በተለይ ደግሞ የአሜሪካ ተምች ሳይቀር ማሳቸው ላይ እንዳይታይ ያደረጉ የልማት አርበኛ በመሆናቸው ስሙ-ገናና አድርጓቸዋል፡፡ የኮነባ ከፊል አርብቶ አደሮችም እዚህ ቦታ ላይ ነበር ሁለት ነገሮችን ትምህርት ለመቅሰም የበቁት፡፡ እነዚህም፡-

1. አርሶአደር ወልደገብርኤል ቤት ውስጥ በተግባር ስልጠና አማካይነት ያዘጋጁት *ፈሳሽ ማዳበሪያ* እዚህ አቶ ገ/የሱስ እርሻ በበቆሎ እና በልዩ ልዩ አትክልቶች (ጎመን፣ ቆስጣ፣ ካሮት፣ ቀይ ስር) ላይ እንዴት ውጤት እንዳመጣ ለመታዘብ በቅተዋል፡፡
2. የተፈጥሮ ፀረ ተባይ አመራረት በተግባር ስልጠና ወስደዋል፡፡ ስልጠናውን የሰጡት አርሶአደር ገብረየሱስ ተስፋይ ከነባለቤታቸው ወ/ሮ ሳባ ጋር በመሆን ነው፡፡ አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ አዘጋጅተው በመቆየታቸው የስልጠናውን ጊዜ አቃልሏል፡፡ ሰልጣኞቹም እያንዳንዷን ግብአት በስም በመጥራት ከአካባቢያቸው ጋር በማገናዘብ እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ የፍየል ሽንት በግመል ሽንት ቢተካ፣ የተለያዩ ቅጠሎች ደግሞ በአካባቢያቸው ያሉትን ለይተው የሌሉትን ደግሞ በተመሳሳይ እንዲተካ፣ ወዘተ የሚል ነበር፡፡

ወ/ሮ ሳራ ምስግና በበኩላቸው ሌላ ዓይነት የፀረ-ተባይ መድሃኒት አዘገጃጀት በተጨማሪ አሳይተዋቸዋል፡፡ ይኸውም አመድ፣ ሳሙና እና ዘይት እሳት ላይ ጥዶ በማፍላት የሚዘጋጅ የፀረ ተባይ አዘገጃጀት ነበር፡፡ ይህም ለተለያዩ ተባዮች መከላከያነት እንደሚውል ተመልክተዋል፡፡

ከእያንዳንዱ የተግባር ስልጠና በኋላ አስገራሚው ነገር ሁሉም ሰልጣኞች አንድም ቀን ችግኝ እናንተ ገዝታችሁ ስጡን ብለው አለማወቃቸው ነው፡፡ በሚጎበኙበት ቦታ ሁሉ የቋሚ ተክል ቀጥተኛ ጠቀሜታው ምን እንደሆነ ማጣራት እና ችግኞችን ሲያዩ እራሳችን እንግዛ ብለው እርስ በራሳቸው ብር ሲበዳደሩ ማየት የተለመደ ነበር፡፡

## ከባህል እና ከሃይማኖት ጋር ሳይጋጩ ሃሳብን ማሳካት እንዲህ ነው

በፕሮጀክት ትውውቅ፣ በመጀመሪያው የትምህርታዊ ጉብኝት እንዲሁም በሁለተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት ጊዜያት አንድም ሴት አልተሳተፈችም ነበር:: ባህሉ ስለማይፈቅድ፡፡ የወ/ሮ ሃረጉን ስራ ከጎበኙና ግንዛቤ ከወሰዱ በኋላ ግን ሴቶች የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ አይተው ስላመኑበት በሩ ሊከፈት ሆነ፡፡ የወ/ሮ ሃረጉ አነቃቂ ንግግርም ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ምክንያቱም ወ/ሮ ሃረጉ እንዳለችው ወንዶች የሚለፉበት ስራ በሙሉ ያለሴት ተሳትፎ እና አስተዋፅኦ ዋጋ የሌለው ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል አስረግጣ ነግራቻዋለችና ነው፡፡ ከዚያም በማስቀጠል ወ/ሮ ሃረጉ አንዳንዶቹን አባወራዎች ሚስቶቻቸው ምን እንደሚሰሩና ምን አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ጠየቀቻቸው፡፡ እነሱም ሲመልሱ ሚስቶቻቸውን ሲያማክሯቸው ደስ ብሏቸው እንደሚሰሙ እና እንደሚሰሩ ነገሯት፡፡ በመቀጠልም ወ/ሮ ሃረጉ ሴቶቹ በአይናቸው ቢያዩ ደግሞ ምን ያህል እንደሚደሰቱና በተሻለ አኳሃን ሊሰሩ እንደሚችሉ አስረዳቻቸው፡፡

አስከትላም፡- “ሌላ ጊዜ ምን እንደሰራችሁ በአካል መጥቼ አይላችኋለሁ፤ ሆኖም ግን በቅድሚያ ሚስቶቻችሁን በመያዝ አብራችሁ ብትጎበኙ ስራችሁ የተሻለ ይሳካላችኋል” በማለት ግብዣ አቀረበችላቸው፡፡ በዚሁም አኳኋን የሴቶች ተሳትፎ በር ተከፈተ፡፡ በመቀጠል ሴቶች እንዴት ይምጡ የሚል

ጥያቄ ትልቅ አጀንዳ ሆነ። ወንዶች በተለይ ትላልቆቹ (በእድሜና በህይወት ልምድ የበሰሉት) ተስማሙ። "ጉብኙቱ የተሳካ እንዲሆን ግን ሚስት ከባልዋ ጋር ከሆነ ወደ ጉብኙቱ መንቀሳቀስ/ መምጣት ትችላለች" በማለት ውሳኔያቸውን አሰሙ።

ይህም በእርግጥ ከፕሮጀክቱ በጀት አኳያ ሲታይ ከአንድ ቤተሰብ ሁለት ሰዎችን ማምጣት ትልቅ ወጪ ቢሆንም በሩ በመከፈቱ ትልቅ እመርታ ነበር። ይልቁንም የተከፈተውን እድል ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆን "አባወራው በደንብ የሰራ፣ ሴቷም በደንብ የተሳተፈች ማለትም የሰራች፣ የስራ ግንኙነቱን ለማሻሻልና የሰመረ ይሆን ዘንድ ደግሞ አብረው ተመካክረው የሚሰሩ መሆን አለባቸው" ተብሎ ተወሰነ።

# 5. ሶስተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት

የሶስተኛው የትምህርት ጉዞ የሲ-ሙሮቢ-ገላዕሎ ወረዳ ተሳታፊ ሰዎችን ያካተተ ጉብኝት ነበር፡፡ ተሳታፊዎች *የቮይስ ኦፍ ዋይልደርነስ ዴቨሎፕሜንታል ኦርጋናይዜሽን* ሰራተኛ፣ የወረዳው ባለሙያ እና 5 ከፊል አርብቶአደሮች ናቸው፡፡ ሲ-ሙሮቢ-ገላዕሎ ወረዳ በዞን 5 ሲሆን ከሸዋ ሮቢት ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ከወረዳው ውስጥ አንድ ቀበሌ (አይደልሃንገግ) ሰፊ የእርሻ መሬት እና የውሃ ሃብት አላቸው፡፡ ቢሆንም በመስኖ በስፋት የሚያለሙት ግን የትምባሆ ተክልን ነው፡፡ የገበያ ችግር ባይኖርባቸውም እቤት ውስጥ ላሉ እናቶች እና ህፃናት ያለው ጠቀሜታ ግን አነስተኛ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ምርቱን የሚሸጠው እና ገንዘብ የሚቀበለው ባለቤቱ ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘብ ተቀባዩ (አባወራው) ለቤተሰብ ምግብ ዋስትና አስቦ ይሸምታል ወይስ አይሸምትም ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው ግብረመልስ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ነው፡፡

ላለፉት ጥቂት ዓመታት በያሉበት አካባቢ ሆነው የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል የሚያግዙ የተለያዩ ስልጠናዎች የተሰጡ ቢሆንም የተሰሩት ስራዎችና ወደ ተሻለ የአኗኗር ደረጃ ከመሸጋገር አኳያ ሲቃኝ ግን ውጤቱ አያመረቃም፡፡ በመሆኑም ለውጡን ለማምጣት በኮነባ ወረዳ ላይ እንደታየው ተገቢው የስልጠና ስልት የአዳራሽ ውስጥ ስልጠና ሳይሆን የልምድ ልውውጥ መሆኑ ስለታመነበት ነው ይህን 3ኛው ትምህርታዊ ጉብኝት ላይ እንዲሳተፉ ተደርጎ የተዘጋጀው፡፡

በዚህም አማካይነት ስልጠናው ያካተተው የሚከተሉት ቦታዎችን ሲሆን ከዚያ የቀሰሙት ልምድም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡-

1. የአርሶአደር ወልደገብርኤል ድምፁ እርሻ (ለበለጠ መረጃ በክፍል 3.1 ላይ ይምልከቱ)

2. የወ/ሮ ሃረጉ ጎበዛይ እርሻ (ለበለጠ መረጃ በክፍል 3.2 ላይ ይምልከቱ)

3. የአርሶአደር ገ/ሚካኤል ግደይ (አባ ሓዊ) እርሻ

- አርሶአደር ገ/ሚካኤል ግደይ ወይም ቅፅል ስሙ አባ ሓዊ (እሳቱ ወይም የእሳት አባት) በመባልም የሚጠራ ሲሆን በምስራቃዊ ትግራይ ዞን፣ የአብረሃ ወአፅበሃ ቀበሌ ነዋሪ ነው፡፡ አባ ሓዊ በክልሉ ውስጥ የተግባር ሰው ተብለው ከተፈረጁ ሞዴል የቀበሌ አስተዳዳሪዎች እና ገበሬዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚወሳ ታታሪ ሰው ነው፡፡

- የትምህርታዊ ጉዞ ተሳታፊዎች ከጉዞው የተማሩት ሶስት ነገሮች መሆናቸው ተናግረዋል፡፡ እነሱም፡-

1. ሁሉንም ነገሮች ለማሸነፍ ስራ ላይ ማተኮር ወይም ጠንካራ ሰራተኛ መሆን ከአባ ሃዊ ተምረናል ብለዋል፣

2. ኑሮን ለማሸነፍ ወይም ሃብታም ለመሆን የመሬት ስፋት ዋስትና አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አባ ሓዊ በትንሽ መሬት ሁሉም ነገር ማምረት ችሏልና፡፡

3. አባ ሃዊ የውሃ አማራጭ መያዝ ማለት ለቤተሰብ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ ወሳኝነት እንዳለው ያምናል፡፡ ስለዚህ በትንሽ የመሬት ይዞታው ውስጥ ሶስት የውሃ አማራጮችን ለማዘጋጀት በቅቷል፡፡

"በአጠቃላይ ይህ ጉብኝት ለኛ እንደ አባ ሃዊ ለመሆን ትልቅ ወኔ ያስታጠቀን ሲሆን ጠንካራ እንድንሆንም መንገድ ጠራጊ ሆኖ አግኝተነዋል" በማለት የአባ ሃዊ ስራ ጉብኝት ተነሳሽነታቸውን እንዳጠናከረላቸው አብራርተዋል፡፡

4. የኮነባ የትሬንች ጋርደን (ስርጉድ መደብ)

- ኮነባ በጣም ፀሃያማ እና ዝናብ አጠር ወረዳ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ከደጋማው የምስራቅ ትግራይ የሚመጡ ወንዞች አሉ፡፡ ቢሆንም እዚያው አካባቢ መኖር ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭነትን ያስከትላል፡፡ ከዚህም የተነሳ የአካባቢው ህብረተሰብ ከነዚህ ወንዞች ራቅ ብሎ ለመኖር በመገደዱ ህዝቡ በምግብ አቅርቦቱ ረገድ በመስኖ እያለማ የአትክልትና ፍራፍሬ ተጠቃሚ ለመሆን አልቻለም ነበር፡፡ የተሻሻለ ዝርያ የሚያቀርብላቸውና ሙያዊ ድጋፍ የሚደርግላቸው አካል ባያገኙም እንኳን ጥቂት ግለሰቦች በራሳቸው ተነሳሽነት የተወሰኑ ሙከራዎችን ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡
- ለዚህ ያግዝ ዘንድ በፔለም ኢትዮጵያ ሃሳብ አመንጪነት የምርጥ ተሞክሮ ማህበር ትሬንች ጋርደኒንግ የሚባል የአትክልት አተካከልና አመራረት ዘዴ ሞክረዋል፡፡ ምርታማነቱንም በተግባር ለማየት በቅተዋል፡፡ በዚህ ወረዳ እምብዛም እርጥበት በሌለበት ሁኔታ በመሳካቱ እና ተቀባይነት በማግኘቱ በበርካታ የአከባቢው ማሕበረሰብ ዘንድ እየተስፋፋ ይገኛል፡፡



ምስል 11፡- ስርጉድ መደብ (ትረንች ጋርደን)

- የትምህርታዊ ጉብኝቱ ተሳታፊዎች ይሄን በማየታቸው በየራሳቸው ይዞታ ቦታዎቻቸው ለማስፋፋት ጥሩ ልምድ ማግኘታቸውን መስክረዋል፡፡ ምክንያቱም ሰፋፊ ግቢ እያላቸው ሳይገለገሉበት በመቅረታቸው ከንቱ ጊዜያት እንዳሳለፉ በቁጭት ሲገልፁ ስለሚስተዋሉ ነው፡፡

# 6. አራተኛው የትምህርታዊ ጉብኝት

የአራተኛው የትምህርት ጉብኝት/ ጉዞ የሚከተሉት አካላት ያካተተው ነው፡፡ እነሱም፡- የኮነባ ወረዳ ምርጥ ከፊል አርብቶአደር ሴቶች፣ የኮነባ ወረዳ የካቢኔ አባላት፣ በኮነባ ወረዳ ውስጥ ጥሩ የስራ ተሳትፎ ያላቸው ወጣቶች እንዲሁም የፔለም ኢትዮጵያ ታሳቢ አባል ድርጅቶች ናቸው፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች የተጋበዙት የጉብኝቱ ዓላማ በቀጥታ ይመለከታቸዋል ተብለው የታመነባቸው ናቸው፡፡ ይኸውም፡-

## 6.1. ታታሪ ሴት ከፊል አርብቶአደሮች

ከዚህ በፊት ሴቶች ባህሉ ስለማይፈቅድላቸው አለመሳተፋቸው ተጠቅሶ ነበር፡፡ አለመሳተፋቸው የህብረተሰቡ ባህል በመሆኑ ተቀብለው ከመሄድ ሌላ አማራጭ አልነበረም፡፡ ተባእቶቹ በሂደት በጉዳዩ ላይ እንዲመክሩበትና እራሳቸው መፍትሄ እንዲያበጁለት ጉዳዩን ወደ እነሱ ከመግፋት ውጭ ሌላ አማራጭ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ምን እናድርግ ሲባል ሴቶች ለቤተሰብ ያላቸውን አስተዋፅኦ ትልቅ መሆኑን ተባእቶቹ እያመኑበት መጡና ደስ የሚያሰኝ ሃሳብ አቀረቡ፡፡

ይኸውም፡- “በአካባቢው ልማድ መሰረት ሴትልጅ ያለ ባለቤቷ ወይም ቤተሰብዋ ብቻዋን ከቤት ስለማትወጣ ለጉብኝት ባል እና ሚስት አብረው ይሂዱ” የሚል ነበር፡፡ እንዲህም ሆኖ የሚመረጡት ባልና ሚስት ጥንዶች በቤት ውስጥ የተሰጣቸውን የልማት ሃላፊነት በትክክል የሚፈፅሙና ተናበው የሚሰሩ ጠንካሮች መሆን እንደሚኖርባቸው በአፅንኦት ተሰመረበት፡፡ ምክንያቱም ሌላው ማህበረሰብ እንዲከተላቸው ይህ አካሄድ ትምህርት ሰጪ መሆን አለበት ተብሎ ስለተወሰነ በዚህ መልኩ ስምንት ጥንዶች ተመርጡና ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴው ተገባ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ ጃዕፈር የሚባል ከፊል አርብቶአደር "ባለቤቴ ብትታመምም ተመርጣለች፣ ወረዳው የመሰከረልኝ ታታሪ ስለሆንኩኝና እነዛ ምሳሌ የሆኑ አርሶአደሮችን ከተለያየን በኋላ ምን ለውጥ እንዳሳዩ ደግሜ ማየት ስለምፈልግ በራሴ ወጪ ልሳተፍ በማለቱ ብቻው አብሮን ለመሄድ ችሏል።

## 6.2. የኮነባ ወረዳ የካቢኔ አባላት

በኮነባ ወረዳ በትምህርታዊ ጉዞ ላይ ሳይሳተፍ በመስማት ብቻ የአትክልት እና ፍራፍሬ ማልማት የጀመረው ወጣት የመንግስት ሰራተኛ ነው። ዓሊ ደራ ይባላል። በማህበረሰቡ የሚታወቀው በተከራካሪነቱ ነው። ይሰራል ብሎ ያሰበው ሰው አልነበረም። አሁን ግን በልማቱ በመነሳሳት የሁሉም ሰው የዓይን ማረፊያ የሚሆን ቦታ የፈጠረ ጀግና ሆኗል። በይዞታው ላይ አትክልቶችን በማምረት ለገበያ መሸጥ ጀምሯል። በርካታ ሰዎች እየመጡ የእርሱን እርሻ ይጎበኙታል፤ በተደጋጋሚ ከጎበኙት መካከልም በዚያን ጊዜ የኮነባ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበረው አብሮ አደጉ አቶ መሐመድ (እንድሪስ) ይገኝበታል።



ምስል 12፡ የዓሊ ደራ እርሻ በከፊል

መሐመድ ኢድሪስ የአሊደራን ስራ በቅጡ ካስተዋለ በኂላ "ለምን እኔስ ለሌላው ሞዴል አልሆንም" በማለት ተነሳሳ፤ "እኔም መስራት እፈልጋለሁኝ" በማለት ኑሩሁሴንን እና ዓሊደራን አማከረ፡፡ ከዚያም ሶስት መደብ አዘጋጀና ማልማት ጀመረ፡፡ ውጤታማ ስራ ለማከናወን በመብቃቱም ሰው እየመጣ ይጎበኘው ጀመር፡፡ ከዚህ በመነሳትም የኮነባ ወረዳ ካቢኔ በሙሉ መስራት እንዳለባቸው ተማመኑ፡፡ የካቢኔ አባላቱም "እኛ ለህዝባችን ሞዴል ሆነን ህዝባችንን በልማት እንምራው!" የሚል የፀና የጋራ ውሳኔ በመወሰን ለስራ ቆርጠው ስለተነሱ የተወሰኑትን የካቢኔ አባላት ከአርብቶ አደሮቹ ጋር በመሆን እንዲጎበኙ ተደረገ፡፡ እንዲያም ሆኖ ለጉብኝቱ መርሃግበር የቢሮ መኪና መያዝ እንደሌለባቸውና ከተቀሩት የጉብኝቱ ተሳታፊ ወገኖቻቸው ጋር አብረው በአውቶቡስ እንዲጓዙ ስምምነት ላይ ተደርሶ ፕሮግራሙ በታቀደው መሰረት አንዲከናወን ተደርጓል፡፡

## 6.3. በኮነባ ወረዳ ውስጥ ጥሩ የስራ ተሳትፎ ያላቸው ወጣቶች

ኮነባ ወረዳ እንደሌሎች አካባቢዎች ሁሉ ቀላል የማይባል የስራ አጥ ወጣት ቁጥር አለ፡፡ ይህን ያህል ከፍተኛ መጠን ላለው ወጣት ሁሉ የስራ እድል ማመቻቸትና ችግሩን ሙሉ በሙሉ መቅረፍ በወረዳው እና ክልሉ ዓቅም ብቻ አዳጋችና በጣም ከባድ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በልዩ ልዩ ስራዎች የተሰማሩ አንዳንድ ወጣቶች ውጤታማ ሲሆኑ ማየት የተለመደ ነው፡፡ በኮነባም የተወሰኑ ወጣቶች ከወላጆቻቸው ጋር የእርሻ እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም እራሳቸውን ችለው በእርሻ ስራ መሰማራት እንደሚችሉ ያላቸው ግንዛቤ እጅግ የደከመ ነው፡፡ ስለዚህ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚገኙትን ውጤታማ ወንድና ሴት ወጣት አርሶአደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች የመመልከት ዕድሉን ካገኙ

ግንዛቤያቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ በማለት ነው እንዲሳተፉ የተደረገው፡፡ ምክንያቱም ከመካከላቸው ከፊሎቹ እንኳን ቢሳካላቸው ለሌሎች ጥሩ አርአያ እና አስተማሪ መሆን እንደሚችሉና በሂደት እየሰፋ ሊሄድ እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ ነበር የተካተቱት፡፡

## 6.4. የፔለም ኢትዮጵያ ታሳቢ አባል ድርጅቶች

ፔለም ኢትዮጵያ ኔትወርክ ነው፡፡ አሁን ያሉት አባላት ብዛት ጥቂት በመሆናቸው ተጨማሪ አባላት እንዲኖሩት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ስለዚህ ሶስት ድርጅቶች አባል ከመሆናቸው በፊት የፔለም ኢትዮጵያ አባል ድርጅቶች ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ምን እንደሆኑ በአካል ተገኝተው በስራዎቹ ላይ ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ልምድ እንዲካፈሉ ሲባል የታደሙ ናቸው፡፡

## 6.5. የተጎበኙ ቦታዎች

በዚህ የትምህርታዊ ጉዞ ተሞክሮን ለማካፈል/ትምህርት ለመቅሰም ያስችላሉ ተብለው የተመረጡና የተጎበኙ ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. መቐለ አካባቢ በገረብ ግባ ዙርያ የሚገኝ የፓፓያ እርሻ - አስጎብኚ ወንድ
2. የአርሶአደር ወልደገብርኤል ድምፁ እርሻ - አስጎብኚ ወንድ
3. ሃለቃ ግደይ ሓጎስ ቤተሰብ - አስጎብኚ ወንድ እና ሴት
4. ወ/ሮ መድህን ገ/ሄር - አስጎብኚ ሴት
5. አርሶአደር ገ/የሱስ ተስፋይ ቤተሰብ - አስጎብኚ ወንድ እና ሴት
6. የወ/ሮ ሃረጉ ጎበዛይ - አስጎብኚ ሴት
7. ዓዲሓ - አስጎብኚ ወንድ እና ሴት

8. የኮነባ የትሬንች ጋርደን (ስርጉድ መደብ) - አስጎብኚ ወንድ

## 6.6. ከትምህርታዊ ጉብኝቱ የተቀሰመው ትምህርት

አጠቃላይ ከትምህርታዊ ጉብኝቱ የተገኙ ዋና ዋና ልምዶች ተብለው በተሳታፊዎች የሰጡት አስተያየቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በመቐለ ዙርያ ገረብ ግባ ወንዝ አጠገብ ከሚገኘው የፓፓያ እርሻ የተማርነው ነገር ቢኖር የፓፓያ አተካከል፣ አያያዝ እና ውሃ እንዴት እንደሚጠጣ ሲሆን በተጨማሪም አንድ የፓፓያ ተክል ምን ያህል ፍሬ እንደሚይዝ ለመገንዘብ ችለናል፡፡



ምስል 13፡- የግባ ወንዝ ዳር የተጎበኘ ፓፓያ

2. ከአርሶአደር ወልደገብርኤል ድምፁ እርሻ የተማርነው ማንኛውም መሬት አላህ ሲፈጥረው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ምንም አስቸጋሪ መሬት ይሁን የሰው ጥረት ከታከለበት መለወጥ እንደሚችል ከዚህ ተምረናል፡፡

3. ከሃለቃ ግደይ ሓጎስ ቤተሰብ የተማርነው ደግሞ፡- አንደኛ እንስሳት በማዳቀል የእንስሳት ምርት ውጤት ምን ያህል ማሳደግ እንደሚቻል፣ ሁለተኛ የቨርሚ ኮምፖስት አዘገጃጀትን እና ሶስተኛ የጓሮ አትክልት አያያዝን ነው፡፡

የመሬት ይዞታችን ምንም ያህል ትንሽ ቢሆን በቤታችን ዙርያ ብዙ ነገር ማምረት እና ቤተሰብ መመገብ እንደሚቻልም ተመልክተናል፡፡

4. ከወ/ሮ መድህን ገ/ሄር የተማርነው የሴት ጥንካሬ ከምን እንደሚጀምር እና የሴቶች ጥንካሬ ለልጆች፣ ለቤተሰብ እና ለማህበረሰብ እንደሚተርፍ ነው፡፡ አሁን ያላቸው እርሻ ተረጋግተው እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ሲሆን፤ የተፈጥሮ የተባይ መከላከያ ዘዴ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለውም አሳይቶናል፡፡ በወ/ሮ መድህን እርሻ ያየነው የቡና ተክል ፍሬው መሸከም እስኪያቅተው ድረስ አፍርቷል፡፡ ስለሆነም የቡና ተክል በቂ ውሃ ካገኘ አመት ሙሉ ፍሬ መስጠት እንደሚችል ለመመልከት ችለናል ብለዋል፡፡



ምስል 14፡- የወ/ሮ መድህን ቋሚ አትክልት እርሻ

5. ከአርሶአደር ገ/የሱስ ተስፋይ እና ከባለቤቱ ወ/ሮ ሳባ አማረ የተማርነው ነገር ቢኖር ፈሳሽ የተፈጥሮ ማዳበሪያ እና የተባይ መከላከያ አሰራር፣ አጠቃቀም እና ውጤቱን አይተናል፡፡ በዚህ ቤተሰብ ያየነው የጎመን እርሻ ምንም ተባይ የማይታይበት በጣም ንፁህ እና ለአይን ማራኪ ነበር፡፡ እንዲህም ለመሆን የበቃው በፈሳሽ ማዳበሪያ ተጠቅመው የተከሉት እና ከተባይ የተከላከሉት በመሆኑ ነው፡፡

6. ከወ/ሮ ሃረጉ ጎበዛይ የተማርነው የሴት ጥንካሬ ወሰን የለውም የሚያስብል ነው። አሁን ያለው እርሻ በጣም ሃብታም ኢንቨስተሮች የሚሰሩት ዓይነት ሲሆን የወ/ሮ ሃረጉ ወኔ የሚያስደንቅ ነው። እርሻው ንፁህ፣ አጅግ የሚማርክ፣ በሴትነትዋ የሚኮራባት እንዲሁም ማንም ሰው በስራዋ ቅናት አድሮበት እንደሷ ለመስራት ጉጉት እንዲያድርበት የሚያደርግ ስራ ነው። በአጠቃላይ ስራዋ ሁለገብ እና አስገራሚ ነው።

7. ዓዲሓ ቀበሌ ያየነው ብዙ ቢሆንም አንዱ የተማርነው ነገር ቢኖር ችግኝ በግለሰብ ደረጃ ማዘጋጀት እንደሚቻል ነው። እዚህ ቦታ የተደራጁ ወጣቶች ችግኝ ማፌያ ጣብያ እና ብዙ የግል የብርቱኳን ችግኝ ማፌያ በማየታችን ‘እኛስ እንዲህ አይነቱን ማዘጋጀት ምን ይገደናል‘ የሚል ስሜት ቀስቅሶብናል።



ምስል 15፡- የአዲሓ የገበሬዎች የብርቱኳን እርሻ

8. ከኮነባ የትሬንች ጋርደን (ስርጉድ መደብ) አሰራር የተማርነው ደግሞ ይህ አሰራር በማንኛውም ዝናብ አጠር አካባቢ ውጤታማ የሆነ አሰራር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በማለት በርካታ ተሞክሮዎችን እንደተካፈሉና ትምህርቶችን እንደቀሰሙ መስክረዋል፡፡

## 6.7. እንደ ማጠቃለያ የተደረጉ ውሳኔዎች

ከትምህርታዊ ጉብኝቱ በኋላ እንደመደምደሚያ በግል እና በወል የተወሰዱ የማጠቃለያ ሃሳቦች እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

- ሁለት ሰዎች ከሬሾ ቀበሌ በግል የመንደሪን እና ጣፋጭ ብርቱካን ችግኝ ለማዘጋጀት ወስነዋል፡፡
- ሁሉም የትምህርታዊ ጉብኝቱ ተሳታፊዎች በቤተሰብ ደረጃ በየቤታቸው ባል እና ሚስት ስራ እየተጋሩ የተሻለ ስራ እንደሚያከናውኑ ቃል ገብተዋል፡፡
- የወረዳው ካቢኔ አባላትም ስራውን ግንባር ቀደም ሆነው ስራውን እንሚያስተገብሩ ያላቸውን ፅኑ አቋም አስታውቀዋል፡፡
- የወረዳው ካቢኔ የፕሮጀክት ቀበሌ ሊቃነ-መናብርትን በመጥራት የሚከተለውን ወስነዋል፡፡
  - ✓ የፕሮጀክቱን ሁኔታ ለማወቅ እንዲረዳን የመረጃ አያያዝ እና የክትትል አስፈላጊነት ቀርቦ መረጃው በወረዳ፣ በቀበሌ እና በህብረተሰብ ደረጃ እንዲደረግ ተወስኗል፤
  - ✓ "በወረዳችን ስድ ግጦሽ ስላለ የቤት እንስሳት ልማቱን እያበላሹ ስለሆነ ስለአጥር ጉዳይ አንድ መላ ልናመጣ ይገባል" ብለዋል፡፡ ለዚህ መፍትሄ

ይሆን ዘንድም፡- "የጋብዮን አጥር በአካባቢው እንዲገኝ ማድረግ፣ ለአጥር የሚሆን የኮሽም ችግኝ ወይም ዘር ፈልጎ መትከል፣ እንደ ቆንጥር የመሳሰሉትን ደግሞ ወደ አካባቢው ማስገባት፣ እንዲሁም በሽቦ አጥር ከልሎ ማስጠበቅ ይገባል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ የኛ ማህብረሰብ አጥር ለማጠር ብዙ ዛፍ ስለሚቆርጥ ከዚያ ይልቅ በከተማ ላይ እንደምናየው ብረት እና ሲሚንቶ ተጠቅመን ቋሚ አጥር ሰርተን ብንከልል ይሻላል፡፡" በማለት ዝርዝር የመፍትሄ ሃሳቦችን አስቀምጠዋል፡፡

- ✓ ህብረተሰቡ የችግኝን ጥቅም ስላየውና ፍላጎትም ስላደረበት ብዙ ችግኝ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ሆኖም ራቅ ወዳሉ ቦታዎች እየተጓዘ የሚያመጣቸው ችግኞች መጠን እጅግ አነስተኛ ስለሆነ በወረዳው ችግኝ ጣብያ ማቋቋም እጅግ አስፈላጊና የማይታለፍ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ በወረዳው፣ የምርጥ ተሞክሮ ማህበር እና መቐለ ዩኒቨርሲቲ ትብብር እየተከናወነ ከሚገኘው ችግኝ ጣብያን የማቋቋም ጅምር ስራ እየተከናወነ የሚገኝ ቢሆንም ከዚሁ በተጓዳኝ ፕሮጀክቱ የተወሰኑ ግለሰቦችን አሰልጥኖ የማቋቋሙን ስራ ቢያስጀምር ማህበረሰቡን ይበልጥ ተጠቃሚ ያደርገዋል፤ ክንውኑንም የተሳለጠ እንዲሆን ያግዛል" የሚል ሃሳብ ከተሳታፊዎቹ ቀርቧል፡፡
- ✓ በወረዳው የሚገኘው የስራ-አጥ ወጣት ብዛት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ አልፎ አልፎ በተናጠልም ይሁን በቤተሰብ ደረጃ ስራ ለመስራት የሚጣጣሩ ጥቂት ወጣቶች ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም ከነዚሁ መካካል የተወሰኑ ወጣቶችን እንደብሎኬት

ማምረት፣ ህንፃ ግንባታና አጥር ማጠር፣ ሱቅ፣ ቁፋሮና የመሳሰሉ ሙያዊ ስልጠናዎችን በመስጠት ብሎም በአነስተኛ መነሻ ካፒታል በማቋቋም በፈረስ ደገምም ሆነ ኮነባ ለሚገኙ የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ቢደረግ ህብረተሰቡን ያግዛሉ ለሌሎችም አርአያ ይሆናሉ፡፡

- ✓ "የጎርፍ አደጋ በየጊዜው ችግር እያመጣ ስለሆነ ጥንቃቄ እና መከላከል ላይ በማተኮር እንዲሁም ተጨማሪ መስኖ በመስራትና ልማት ላይ እንዲውል በማድረግ አደጋውን ብንቀንሰው ይሻላል" ብለዋል፡፡

በተጨማሪ ለዚህ ሁሉ ነገር መሳካት ግን ሁለት ነገሮች እንዲቋቋሙ ሃሳብ ቀርቧል፡፡ እነሱም፡-

- ✓ 1 የፕሮጅክቱ ስኬት እና የተጠቃሚዎች ፍላጎት እና የመሳሰሉትን እንዲከታተል ከማህበረሰብ የክትትል ኮሚቴ እንዲቋቋም፡፡
- ✓ 2 ሁልጊዜ ማንኛውንም ነገር ከፕሮጀክት ወይም ከመንግስት፣ ከሌላ ባለሙያ ከምንጠብቅ በአቅራቢያ የሚሰራ የወጣቶች የህብረት ስራ ማህበር ወይም የሽርክና ማህበር እንዲቋቋም ተብሏል፡፡

# 7. የፕሮጀክቱ ዘላቂነት ምን ይመስላል

የችግኝ አቅርቦቱ በሶስት መልክ ነበር፡፡ እነሱም፡-

## 7.1. የችግኝ አቅርቦት ቀላል እና ተደራሽ ማድረግ

ፕሮጀክቱ ለመጀመርያ ጊዜ ማለትም በ2010 ዓ.ም 334 ያህል የተለያየ የቋሚ አትክልት ችግኝ ገዝቶ አከፋፍሏል፡፡ የተከፋፈለው ችግኝ ዓይነት ፓፓያ፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ እንዲሁም የሸንኮራ እና የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ተከፋፍሏል፡፡ ሌላ ደግሞ 300 ያህል የፓፓያ ችግኝ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ በስጦታ መልክ አግኝተን አከፋፍለናል፡፡ የህብረተሰቡ ክፍል ደግሞ በራሳቸው ተነሳሽነት የበለጠ (380) ገዝተው ተጠቅመዋል፡፡ በቀጣዩ ዓመት (2011) ደግሞ ሌሎች የበለጠ ሲያቀርቡ የህብረተሰቡ ገዝቶ የመጠቀም ተነሳሽነት እያነሰ ሄዷል፡፡ ለበለጠ መረጃ ሰንጠረዥ 1 እና 2 ይመልከቱ፡፡

### 7.1.1. የሕብረተሰቡ የተደራጀ የችግኝ አቅርቦት

ድርጅቱ በቁሳቁስ ማሟላት፣ ስልጠና እና ልምድ ልውውጥ ከማዘጋጀትና ከማስተባበር በዘለለ ችግኝ ገዝቶ ማቅረብ ላይ ትኩረት መስጠት አልፈለገም፡፡ ለዚህም ዋንኛው ምክንያት የህብረተሰቡ የችግኝ ፍላጎትና እንክብካቤ ደረጃ ተገዝቶ ስለቀረበለት ብቻ ማወቅ አይቻልም፡፡ ይልቁንስ የህብረተሰቡ ትኩረት እና ፍላጎት ማወቅ የሚቻለው እራሱ ምን ያህል ይገዛል፣ ይንከባከባል፣ ምን ያህል ጊዜ ወይም ገንዘብ ያወጣል የሚለውን በተግባራዊ እንቅስቃሴዉ ሊታይ እንደሆነ ያምናል፡፡ እስካሁን በነበረት ጥቂት ጊዚያትም ተጠቃሚዎች አስተባብረው ፓፓያ እና ብርትኳን ገዝተው ተክለዋል፡፡

### 7.1.2. በእያንዳንዱ ጉብኝት በግል ተነሳሽነት የተገዛ ችግኝ

በአጠቃላይ የተካሄዱት ትምህርታዊ ጉብኝቶች በእያንዳንዱ ጉብኝት ላይ የታየው በጣም የሚያበረታታ ነው ምክንያቱም ተጠቃሚዎች በየግላቸው የገዙት ችግኝ ብዛት በጣም ብዙ ነበር፡፡ በተለይ ለማንጎ እና ለብርቱኳን ልዩ ትኩረት ነበር የሰጡት፡፡ ሆኖም ግን እያንዳንዱ ሰው በተለያየ ሁኔታ መረጃ እየሰበሰበ ከቀረበው ችግኝ የተለየም የተከሉ ሰዎች አሉ ለምሳሌ ወይን፣ ቡና፣ ሎሚ፣ ወዘተ፡፡ ስለዚህ ህብረተሰቡ ብዙ ጥረት እያደረገ ነው፡፡

## 7.2. የቤተሰብ ተሳትፎ ማጠናከር

የቤተሰብ ተሳትፎ ሲባል እቤት ውስጥ የሚኖሩ አባላት እቤት ውስጥ ከሚከናወኑት የልማት ተግባራት ውስጥ በምን ያህሉ ላይ ይሳተፋሉ ብቻ ሳይሆን ምን ያህሉንስ በአግባቡ ያዉቋቸዋል ወይም ግንዛቤ አላቸው የሚለውን ያካተተ ነው፡፡ በአፋር ባህል በሚስጥር የሚያዝ ምንም ነገር የለም፡፡ በቤተሰቡ አባላት መካከል ማለትም በሚስት፣ ባል እና ልጅ ወዘተ ይቅርና ማንም አላፊ አግዳሚ ለመጎብኘት ወይም ለመጠየቅ ቢመጣ ማስረዳት ነው እንጂ አይመለከተዉም ተብሎ መረጃዉን ከመስጠት አይታቀቡም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ዘንድ እውቀትን እና ግንዛቤን የሚያሰፋ ይሁን ማናቸዉንም መረጃ መደበቅ እንደነውር ይቆጠራል፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን የወንድ እንግዳ እቤት ሲመጣ ሴት አትገኝም፡፡ ከዛ ባሻገር ማንም የቤተሰብ አባል እቤቱ ውስጥ ስለሚያከናውነው ስራ የማወቅ/ የማሳወቅ መብትም ግዴታም አለበት፡፡ ባጠቃላይ አላውቅም አይባልም፡፡



ስእል 16፡ መሓመድ ዓሊ ዑመር የጓሮ አትክልቱን እንዴት እንዳለ ከህፃናት ጋር ሲፈትሽ እና ለህፃናት ሲያሳይ



ስእል 17፡ መሓመድ ዓሊ ዑመር የጓሮ አትክልት አያያዝ እና ገረዛ ለህፃናት ልጆቹ ሲያሰለጥን

### 7.2.1. የሴቶች ያልታየ አስተዋፅኦ

በብዙ ቤተሰብ እየታየ ያለው ወንድ የችግኝ አተካከል ሰልጥኖ መጥቶ ይተክላል፡፡ ሆኖም ግን ስራው ከቤት አካባቢ ውጪ ካልሆነ በስተቀር የሴቶችን አስተዋፅኦ የሚጠይቅ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እቤት አካባቢ ሲሆን ሴቶች ሲተክል ያያሉ

አንዳንዴ ደግሞ ወንዱ ትንሽ ምክር ቢጤ ይሰጣቸዋል። ከዚያ በኋላ ማጠር፣ መኮትኮት፣ ውሃ ማጠጣት፣ መከታተል፣ ወዘተ የሴቷ ስራ ነው የሚሆነው። በአብዛኛው ወንዶች ስልጠናዉን ቢወስዱም ከችግኙ ተከላ በኋላ ያሉትን እንክብካቤዎችና የስራው ሃላፊነት በሴት እማወራዋ ጫንቃ የሚወድቁ እንደሆኑ የታወቀ ነው። ምክንያቱም ሴቶች እንጅ ወንዶች እቤት አካባቢ አይውሉምና። ለምሳሌ በበልበል ቀበሌ የሚገኘው የጃዕፈርን የቋሚ ተክል እርሻ ለመጎብኘት ስንሄድ አባወራዉ በቦታዉ ባይኖርም ባለቤቱ ከልጆቿ ጋር በመሆን ስትሰራ እና ስትቆጣጠር ነበር ያገኘናት። እንዲያም ሆኖ ግን ከእኛ እይታ ለመራቅ ጥረት ስታደርግ መታዘብ ችለናል።

### 7.2.2. ወንዶች ሴቶች እንዲሳተፉ ያቀረቡት ሃሳብ

ሴቶች ብቻቸውን ከአካባቢያቸው ርቀው ወጥተው እንዲሳተፉ ባህሉ የሚፈቅድላቸዉ ባይሆንም የወረዳው ከፊል አርብቶ አደሮች ግን ፕሮጀክቱ ስኬታማ እንዲሆን ካላቸዉ ፍላጎት የተነሳ የተቻላቸውን ሁሉ አስተዋፅኦ ከማድረግ አልተቆጠቡም። በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት አንድም ሴት እማወራ በልማታዊ ስራዎች እና ልምድ ለመቅሰም ለሚደረጉ ማናቸዉም ትምህርታዊ ጉዞዎች ላይ እንድትሳተፍ ፈቃደኛ አልነበሩም። ይሁንና በአጠቃላይ የልማት ክንዉኖች ወቅት ስራዉ የሴቶች አስተዋፅኦ የሚጫወተው ሚና ለውጭ ተመልካች በግልፅ ባይታይም እዉነታዉ ሲታይ ግን የሚያስገኘዉ ፋይዳ በዋጋ የማይተመን ነበር። ባለቤቷ ሰልጥኖ ወደቤት ሲመለስ መረጃውን በትክክል ያስተላልፍላታል። ከዚያም አልፎ በተግባር ሲሰራ ታያለች። ከዚህ በኋላ ግን የምትከታተለውና ቀጣዮቹን ተግባራት የምታከናዉነዉ እሷው ነች፤ ምክንያቱም እሱ ወደሌላ ቦታ የመንቀሳቀስ እድሉም ሆነ ልማዱ ሰፊ ነዉ።



ምስል 18፡- ሴቶቸ ምንያህል ትኩረት እንደሚሰጡ (ወ/ሮ አሰፋ አስጎብኝ ዓሊደራ ተርጓሚ)

በተጨማሪም የሴቶችን ተሳትፎ ከዚህ የበለጠ ሊያሻሽሉ የሚችሉ ሁለት ምርጥ ሃሳቦች አቅርበዋል፡፡ እነሱም በወረዳው ውስጥ እና ከወረዳ ውጪ በሚሉ ተለይተዉ የቀረቡ ናቸው፡፡

*7.2.2.1. በወረዳው ውስጥ*

- በወረዳው ውስጥ ሲሆን ባህላዊ ተቃርኖ ሳይፈጥሩ ህብረተሰቡን የሚያሳትፉ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ግንኙነቶችን መጠቀም የሚለዉን አግባብ(አካሄድ) ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም በስብሰባው ሴቶች በብዛት ወይም ሴቶች ብቻ የሚገናኙበትን ፕሮግራም ማዘጋጀት፤ ከተቻለ ደግሞ የመስጊድ ኢማም አሰልጥኖ በመስጊድ ውስጥ እንደ ሰርቶ ማሳያ የመሳሰሉ የማስተማሪያ ዝግጅቶችን መጀመር፡፡ ከዚህም የሚገኘዉ መልስ በድህነት ለሚማቅቁና አቅመ ደካማ ለሆኑ የአካባቢዉ ወገኖች ጠቀሜታ እንዲዉል ማድረግ፡፡ ሰርቶ ማሳየዉ በዚህ ስፍራ መዘጋጀቱ ሌላ ተጨማሪ ፋይዳ አለዉ ይኸዉም ሙስሊም የአካባቢዉ ማህበረሰበብ እለተ ከእለት ወደ

መስኪዱ በሚመላለስበት ወቅት እግረ መንገዱን ከሃይማኖታዊ ፀሎት በኋላ እንዲያዩት እና እንዲወያዩበት ምክንያት ይሆናል፡፡

- በተጨማሪም ብዙ ሰዎች በተለይ ሴቶች የሚሰበሰቡበት ወይም የሚገናኙበት ፕሮግራም በሚያጋጥምበት ወቅት ይሄንን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ መስራትና ዋነኛ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፡፡ ለአብነት እርጉዝ ሴት ቤት፣ ገበያ እና የመጠጥ ውሃ የሚከፋፈልበት ቦታ በመለየት መንቀሳቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በአፋር ህብረተሰብ ውስጥ እያንዳንዷ ነገር በፅሞና ትደመጣለች፤ ውይይትም ይደረግባታልና ነዉ፡፡
- ምሳሌ፡- ወ/ሮ መሪየም ዓሊ (የኢድሪስ ሓማድ ባለቤት) በጣም ጠንካራ ሰራተኛ ሴት ነች፡፡ ኑርሁሴን ከወ/ሮ መሪየም ጋር ተማክሮ ሌሎች ሴቶችን ለማሳተፍ ያወጡት እቅድ እንደሚከተለው ነው፡፡ ወ/ሮ መሪየም እርጉዝ ስለሆነች ስትወልድ እቤቷ ድረስ እንደሚመጡ ይታወቃል፡፡ ይህም በሷ ቤት ውስጥ ጉዳዩን ዋንኛ አጀንዳ አድርጋ ለማንሳት መልካም አጋጣሚና በጣም ቀላሉ መንገድ እንደሚሆንላት ግልፅ ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግም ለሴቶች አጀንዳ የሚሆን ምን ምን እናዘጋጅ የሚል ዋንኛ የመወያያ ርዕሰ-ጉዳይ ሆኖ ሲመክሩ ሲዘክሩ ከቆዩ በኋላ ስነ-ምግብ እና የምግብ ዋስትና የአጀንዳው አካል እንዲሆን ሃሳብ ቀረበ፡፡ አመርቂ ውጤትና የላቀ የሴቶች ተሳትፎ የተስተዋለበት መልካም የተጓዳኝ መድረክ ለመሆን በቃ፡፡ ይህን መሰል አጋጣሚ አሟጥጦ በመጠቀም

የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ እንደሚቻና የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ እንዲታሰብ ትምህርት የሰጠ ነበር፡፡

*7.2.2.2. ከወረዳው ውጪ*

- ከወረዳው ውጪ ሲሆን ሴቶች ከባሎቻቸው ወይም ባለቤት እና ወላጅ የፈቀደውን ሰው አብሮ እንዲኖር በማድረግ የሴቶችን ተሳትፎ መጨመር ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ባህሉ እና ስርአቱ ሳይታወቅ የተሳትፎ ጥሪ እና ግፊት ማድረግ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ይህንን አይነቱ አካሄድ ሲያስፈፅሙ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

- ከወረዳው ውጪ በሚሆንበት ጊዜ የሚጎበኙት ቦታዎች (ማሳዎች) ላይ ቢቻል የሴቶች ወይም ማብራሪያ ሰጭዎቹ ሴቶቸ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም የሚናገረው ወንድ ከሆነ ሊያዩት እና ትኩረት ሰጥተው ሊሰሙት ባህሉ ሊያግዳቸዉ ስለሚችል ነዉ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በአስጎብኚው አካባቢም አይቆሙም፡፡ ማለትም አጠገቡ ሆነዉ ለመከታተል ያዳግታቸዋል፡፡ የሚጎበኘው ቦታ የሴት እና ጉብኙቱም በሴቶች ገላጭነት የሚከናወን ከሆነ ግን ዘና ብለው ያያሉ፣ ይጎበኛሉ፣ ይጠይቃሉ፣ ጠጋ ብለው ይቆማሉ፣ ወዘተ፡፡ ይህም በተጨባጭ አጋጥሟል፡፡ ለምሳሌ በሚከተለው ፎቶ ከጀግናዋ ወ/ሮ ሃረጉ ጋር አብራችሁ ፎቶ ተነሱ ሲባሉ ሁሉም ሴቶች እንዴት ደስ ብሏቸው እንደቆሙ እና እንደተነሱ ማየት ይቻላል፡፡ በተጨማሪ በወ/ሮ ሃረጉ የቨርሚ ከምፖስት ቦታ ለብቻቸው (ወንዶች እንዲለቁላቸው ሲደረግ) እንዴት ዘና ብለው እንደተወያዩ መመልከት ይቻላል፡፡

### 7.2.3. የወረዳው ካቢኔ እና የሴቶች ተሳትፎ

ከዚህ ቀደም የወረዳው የካቢኔ አባላት በሞላ ትኩረትና እንቅስቃሴ በአስተዳደራዊ መዋቅራቸው ስር ስለሚገኘው ከፊል አርብቶአደር የልማት ስራ ክንውን እና ተሳትፎ ላይ ነበር፡፡ እራሳቸውን የተሳትፎው አካል ስለማድረግ አስበውት አያውቁም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በተለይም ከስልጠናውና ከምክክሩ በኋላ ግን ይህን መሰሉ አመለካከት በአያሌው ተለውጧል፡፡ ከብዙው በከፊል ለመጥቀስ ያህል፡-

#### *ሀ. ግንባር ቀደሙ የካቢኔ አባል የነበሩ - መሃመድ እንድሪሱ*

አርሶአደር መሓመድ እንድሪሱ የኮነባ ወረዳ አስተዳዳሪ እንዲሁም የካቢኔ አባል የነበረ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ እዚህ ወረዳ ላይ እንዲጀመር አስፈላጊውን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ የእያንዳንዱ ከፊል አርብቶአደር የልማት ስራን ማየት እጅግ ያስደስተው ሰለነበረ አጥብቆ የሚከታተለው ጉዳይ ነበር፡፡ እንዲህም ይላል፡-

> *‘ወጣት ዓሊደራ ጎርፍ የሸረሸረውን መሬት እየቆፈረ ነው’ እያሉ ሲያወሩ ቁምነገር ያለው ይሆናል የሚል እምነት ፈፅሞ አልነበረኝም፤ ይልቁንም የነበረኝ እሳቤና እሰጠው የነበረ ምላሽ ‘ጊዜ ማሳለፊያ ይሆነዋል’ የሚል ነበር፤ አንድ ቀን አንድ ሰው መጥቶ ‘ኸረ የሚሰራው ስራ ከጊዜ ማሳለፊያ ያለፈ ነው’ ሲለኝ ማመን አቃተኝ፡፡ ቢሆንም ማየት ይሻላል በማለት ለጉብኝት ስሄድ ያየሁት ነገር ለማመን የሚከብድ ሆኖ አገኘሁት፡፡ የእርከኑ አሰራር፣ የመደቡ አዘገጃጀት፣ የችግኝ አፈላሉ፣ የቋሚ ተክሉ አተካከል፣ ወዘተ ሳየው እውነት ዓሊደራ እንደሰራው ለማመን ቸገረኝ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ዓሊደራ ምን ያህል የተደበቀ እምቅ ጉልበት*

እና ወኔ እንዳለው ማሰብ ከምገምተው በላይ ሆኖብኝ ነበር፡፡



ምስል 19፡- የወረዳ ካቢኔ ከጉዞ በኋላ ሲገመግሙ

የዓሊደራን ስራ ካየሁኝ በኋላ 'ይህን ወደ ተቀረው ህዝብ እንዴት ማስተላለፍና ማዳረስ ይቻላል?' የሚል ጥያቄ አእምሮዬን ወጥሮ ይዞ እንቅልፍ ነሳኝ፡፡ እየተመላለስኩም እጎበኘው ጀመር፡፡ ሌላ ሰዉ ይህን እንዳይተገብር ምን የሚያግደው ነገር ይኖራል?' እያልኩኝ በማስብበት ወቅት አንድ ሃሳብ ብልጭ አለልኝ፤ 'እኔው ራሴስ ብሆን ምን ጎደለብኝ? ለምን በራሴ ቦታ ላይ አልጀምርም?' የሚል፡፡ ለማገናዘብና ለመወሰን አንድ ሁለት ቀን ፈጀብኝ፡፡ በመጨረሻ ግን እኔ ለመተግበር የጎደለኝ ነገር መወሰን ብቻ መሆኑን ተገነዘበኩ፡፡ ሌላውም ሰው ቢሆን እንዲሁ፡፡ እናም ስራውን ለመተግበር ቁርጥ ውሳኔዬን አሳረፍኩ፡፡

ወደ ወጣቱ ዓሊደራ ሄጄ ውሳኔዬን ገልጬ ጅምር ስራዎቹ ላይ እንዲያግዘኝ አማከርኩት፡፡ ሆኖም

እንደምተገብረው ስላላመነ ብዙ ጥያቄ ጠየቀኝ፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፡-

1. ስራው ብዙ ጉልበት ይፈጃል አንተ ደግሞ ብዙ የሰው ሃይል የለህም፡፡
2. ስራው ብዙ ጊዜ ይፈልጋል አንተ ደግሞ ጊዜህን በመንግስት ቢሮ ነው የምታሳልፈው፡፡
3. ስራው ብዙ ወጪ ይፈልጋል አንተ ደግሞ ብር የለህም፡፡ አለኝ፡፡

እኔ ግን ወስኜ ስለነበር በምንም መልኩ መስራት እንደምፈልግና ቆርጬ መነሳቴን አስረዳሁት፡፡ በዚህ መልኩ ከዓሊደራ እና ኑሩሁሴን ጋር በመሆን በቂ ዝግጅት አደረግን፡፡ ሶስታችንም በኔ ግቢ ውስጥ ለተከታታይ ቀናት ስንሰራ አሳለፈን፤ እኔን የፈለገ ሰው እቤቴ ሲመጣም ስራችንን ያይና ጥቂት ካወያየን በኋላ ስራ እያገዘን ሲሄድ ስራውን በፍጥነት ጨረስን፡፡

ቦታውን ከአዘጋጀን በኋላ የደረሰ የቆስጣ፣ ሰላጣ፣ ቃርያ ችግኝ ተከልንበት፡፡ አሁን እራሱ በአካል ጉብኝቱ ቦታ ላይ ብሆንም ልቤ እቤቴ ውስጥ ከአትክልቶቼ ጋር ነው፡፡ እንደ ልጄ ነው የምሳሳላቸው፡፡ ዓሊደራ እርሻ ቦታው ላይ ይደበቅ የነበረው ሚስጥሩ የገባኝ አሁን ነው፡፡

### *ለ. የመጀመሪያው የሴቶች ቡድን*

በመጀመሪያው የሴቶች ስብስብ በጣም አስገራሚ ነገር ታዘብን፡፡ የባህል እና የእምነት ጉዳይ ሆኖ ሴቶች ሃሳብ የመስጠት ተነሳሽነታቸው አነስተኛ ቢሆንም አዳዲስ ሃሰቦችን በፍጥነት የመገንዘብና የጭንቅላታቸው የመያዝ ችሎታ ግን በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህንን የተገነዘብነው ጉዞ ላይ እያለን

በተደረገው የሴቶች ጥያቄና መልስ ዝግጅት ላይ ነበር፡፡ አልተከታተሉትም ወይም አያውቁት ይሆናል ብለን የምንገምታቸው ነገሮች/ጉዳዮች ሳይቀር በሚገባ ሲገልፁት አስተዋልን፡፡

በአውቶቡስ ውስጥ በነበረው የጥያቄ እና መልስ ውድድር ጊዜ ወንዶች እና ሴቶች እንዲመካከሩ እና እንዲያስረዱዋቸው ተስማማን፡፡ በዚህ ሁኔታ ለማወቅ የፈልግነው እርስበርሳቸው ይተጋገዙ እና በአግባቡ ይከታተሉ እንደሆን ለመለየት ነበር፡፡ ሆኖም ሴቶች ሲመልሱ ወንዶች ሊያግዟቸው ፈልገው ሲናገሩ “አውቀዋለሁኝ” እያሉ ይመልሱላቸው ነበር፡፡ ይህም ሴቶቹ በፍላጎት እና በትኩረት ይከታተሉ እንደነበር ያሳያል፡፡



ምስል 20፡- የመጀመሪያው ተጓዥ የሴቶች ቡድን ከወ/ሮ ሃረጉ ጋር

## 7.3. ወደ ዘላቂ የችግኝ አቅርቦት ጉዞ ከነ አማራጩ

### 7.3.1. በችግኝ ጣብያ ማቋቋም ላይ የተደረገ አሳታፊነት

የኮነባ ወረዳ ህዝብ የችግኝ አቅርቦት ፍላጎት እየጨመረ መሄድ ጀመረ፡፡ የሚፈለገው የችግኝ ዓይነት የሚገኘው ደግሞ በትግራይ ክልል በተለይም በመቐለ፣ ቆላ ተንቤን፣ አላማጣ፣ ውቅሮ ወይም ራማ አከባቢዎች ላይ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከሌላ ቦታ እየገዙ እያጓጓዙ የህብረተሰቡን ፍላጎት ማሟላት እንደማይቻል ደግሞ ለማንም ግልፅ ነው፤ ይህም

በመሆኑ የችግኝ ጣብያ አስፈላጊነት ጥያቄ ከግለሰብና ከባለሙያው አልፎ የወረዳው ባለስልጣኑም ጭምር እየሆነ መጣ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለን ሁለት አስደሳች ተስፋዎች ተከሰቱ፡-

**አንደኛው፡-** በፕሮፌሰር ምትኩ ሃይሌ ጋባዥነት የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ክንደያ ገ/ህይወት ኮነባ ወረዳ የሚገኘውን የልማት ስራ ሊጎበኙ መጥተው ነበር፡፡ የልማት ስራውን ጎብኝተው ሲጨርሱ ደስ በመሰኘታቸው በቅድሚያ ከፊል አርብቶ አደሮችን፣ ቀጥሎ ደግሞ የወረዳው መስተዳድርን ‘ምን እንድናግዛችሁ ትፈልጋላችሁ?’ በማለት ጥያቄያቸውን ሰነዘሩ፡፡ የህዝቡም የመስተዳድሩም ሃሳብ በአንድ ድምፅ ችግኝ ጣብያ ማቋቋም የሚል ሆነ፡፡ በጣም ኩራት እንዲሰማን ያደረገው የፕሮፌሰር ክንደያ ግልፅ መልስ ነበር፡፡ “እናግዛቹኋለን!” ነበር ያሉት፡፡

በዚህ ሁኔታ የችግኝ ጣቢያ ለማቋቋም የስራ ክፍፍል ተደረገ፡፡ የስራ ክፍፍሉና ሃላፊነት እንደሚከተለው ነበር፡፡

- **የኮነባ ወረዳ መስተዳድር** - ለችግኝ ጣብያ የሚሆን ቦታ በመምረጥ እንዲያዘጋጅ እና ያለበትን ደረጃ በፍጥነት ለመቐለ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ለፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም እና ምርጥ ተሞክሮ ማህበር በፅሁፍ እንዲያሳውቅ፡፡
- **የመቐለ ዩኒቨርሲቲ**

  - ለሚመለከተው አካል መመሪያ እንዲሰጥ እና ስራውን የሚከታተል ሰው እንዲመድብ፣ እንዲሁም

  - የችግኝ ጣብያውን ስራ ለማስጀመር የሚያስችል አስፈላጊ ዝግጅት እንዲያደርግ፤

ማስታወሻ፡- ከስራ ክፍፍሉ በኋላ የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ሁለት (የችግኝ ጣብያ እና የቋሚ አትክልት) ባለሙያዎች በመመደብ ክትትል እና ለወረዳው ባለሙያዎች ምክር እየለገሱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ አካባቢዎች ለኮነባ የሚሆኑ የቋሚ አትክልቶች ችግኝ እያሰባሰቡ ናቸው፡፡

- **ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም/ ምርጥ ተሞክሮ ማህበር**

  - የችግኝ ጣብያውን እንቅስቃሴ ማህበረሰብ ተኮር እንዲሆን በኤክስቴንሽን ስራ ላይ እንዲያተኩርና መሰረቱን እንዲያነጥፍ፤

  - ከኮነባ ወረዳ እና ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የማስተባበሩን ስራ በሃለፊነት ማከናውን፡

ማስታወሻ፡- ከስራ ክፍፍሉ በኋላ ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም በራስ ተነሳሽነት ከምርጥ ተሞክሮ ማህበር ጋር በመተባበር የችግኝ ጣብያውን ቁሳቁስ በመግዛት ለማሟላት ጥረት አድርጓል፡፡

**ሁለተኛው፡-** የስራ ክፍፍሉ በእንዲህ መልኩ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የወረዳው መስተዳድር ከወረዳው በጀት ላይ ቅድሚያ በመስጠት ለችግኝ ጣቢያው የሚሆን 1.5 ሚሊየን ብር ከመመደቡም ባሻገር ከአርብቶ አደር ፅ/ቤት እና ከወረዳው ውሃ ሃብት ፅ/ቤት ጋር በመሆን ለችግኝ ጣብያው የሚሆን ቦታ በመለየት አሳውቋል፡፡ በወርሃ የካቲት እስከ ሰኔ 2011 ዓ.ም. ድረስ የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ቁፋሮ እና አጥር ስራ እንዲፋጠኑ አድርጎ አጠናቋል፡፡ ከዚያም አልፎ ለችግኝ ማፍያ የሚሆን መደብ እንዲሁም ለማዳቀል ግልጋሎት የሚውሉ ቋሚ ተክሎች የሚተከልባቸው ጉድጓዶችንም እንዲዘጋጅ አድርገዋል፡፡

እንዲህም ሆኖ ማናቸውም በትብብር የሚከናወን ስራ ሲሰራ ትእግስት መጠየቁ የማይታበል ሐቅ ነው፡፡ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ስራቸውን በተገቢው መንገድ ቢሰሩም በህብረተሰቡ እይታ ግን ሂደቱ የተፋጠነ ተደርጎ አልተቆጠረም ነበር፡፡ ምክንያቱም ህብረተሰቡ በዚሁ ዓመት የደረሰ ችግኝ ከችግኝ ጣብያው በበቂ ሁኔታ መውሰድ ይፈልግ ስለነበረ ነው፡፡

## 7.3.2. ትልቅ ሃሳብ በትንሽ ስራ ይጀመራል፣ ትልቅ ዛፍ ከትንሽ ዘር ይፈጠራል

በጥር ወር 2011 ዓ.ም. ሴቶችን ይዘን ስንጓዝ የሃረጉ ጎበዛይ የማንጎ ችግኝ እና የዓዲሓ የግለሰቦች የብርቱኳን ችግኝ ዝግጅት ከጎበኙ በኋላ ችግኝ መንግስት እንጂ እንዴት ግለሰብ ሊሰራው ይችላል ብለው ጠይቀው ነበር፡፡ ሁኔታውን ከተረዱ በኋላ ግን ያላቸው ፍላጎት የተለየ ነበር በተለይ አርብቶአደር ሑሴን መሓመድ ሽሪፍ ያሳዩት ከፍተኛ ፍላጎትና መነሳሳት በተለየ ሁኔታ ትኩረታችንን ሳበው፡፡ ከፊል አርብቶአደር ሑሴን ችግኝ ለማዘጋጀት ምን ምን እንደሚያስፈልግ መጠየቅ ጀመረ፤ መልስ በአጭሩ ቢነገረውም ጥያቄውን ከመደጋገም አልቆጠብ አለ፡፡

ቃለ ምልልሱ እንደሚከተለው ነበር፡፡

- ጥያቄ፡- መጀመሪያ ምን ያስፈልጋል?
- መልስ፡- "መጀመሪያ ፍላጎት ያስፈልጋል"፡፡
- እሱም፡- "በጣም ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ" አለን፡፡
- ቀጥሎ "ችግኝ ለማዘጋጀት ቦታ እና ውሃ ያስፈልጋል" የሚል ሃሳብ ተሰነዘረ፡፡
- እሱም፡- "በአካባቢዬ የሚያልፍ ከደጋው የሚወርድ ትንሽ ወንዝ አለ ቦታም አለኝ" አለ፡፡
- ቀጥሎ "ለመሰረተ ግንድ የሚሆን የሎሚ ወይም የኮምጣጤ ፍሬ ያስፈልጋል" ተባለ፡፡
- መልስ "ኮምጣጤም ሎሚም አለኝ" አለ፡፡

- ቀጥሎ "ለማዳቀል የሚሆን ጣፋጭ ብርትኳን ያስፈልጋል"፡፡
- እሱም "ከጉንዳጉንዶ ገዳም የመጣ ብርቱኳን እና መንደሪን አለኝ" ሲል መለሰ፡፡
- ቀጥሎ "ለመስሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ" ሲባል፤
- እሱም፡- "ቁሳቁሶቹ እንዴት ያሉ ናቸው? እኔስ ማግኘት እችላለሁኝ ወይ?" በማለት መልሶ ጠየቀ፡፡
- እኛም፡- "ዋና ዋናዎቹ ማዳቀያ/ መክተቢያ ምላጭ፣ ችግኝ እና ቅርንጫፍ መቁረጫ መቀስ፣ መቆፈርያ፣ ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በገበያ ሊገኙ ይችላሉ፣" በጣም ውድ አለመሆኑንም ጭምር ተነገረው፡፡
- በማስከተል "የአዘገጃጀት እና የማዳቀል ችሎታ ያስፈልጋል" ስንለው፡ ጥያቄውን በጥያቄ ነበር የመለሰው "የተማረ ሰው ነው የሚችለው ወይስ እንደኔ ያልተማረ ቢሰለጥንም ይችለዋል?" አለ፡፡
- መልስ "አዎን ባይማርም በስልጠና ይችለዋል፡፡ ዋናው በሞራል መሰልጠን ነው የሚያስፈልገው፣ ምሳሌ ዓዲሓ ላይ ያየናቸው ሰዎች እኮ ሁሉም የተማሩ ናቸው ማለት አይደለም፡፡"
- በመጨረሻ እንዲህ ነበር ያለው "ስለዚህ እኔ እንደነሱ መሰልጠን የምችል ከሆነ ደህና ሰው ጋር አገናኙኝ፣ አንዴ ካየሁኝ አይጠፋብኝም" ነበር ያለው፡፡

ስለዚህ ትልቅ ዛፍ ከትንሽ ዘር እንደሚፈጠር ትልቅ ሃሳብም በትንሽ ስራ ይጀመራል፡፡ ስለዚህ ይህ ሃሳብ በዚህ ሞራል ይሳካል" አልን፡፡ አስተማሪም እንደሚሆን ተመኘን፡፡ አይናችንንም ጣልንበት፡፡

ትልቅ ሃሳብ በትንሽ ስራ ይጀመራል ማለት ትልቁን ችግኝ ጣብያ እስኪያልቅ ከመጠበቅ ፍላጎት ባለው ሰው ወይም ባላቸው ሰዎች መጀመሩ ብዙ ጥቅም አለው፡፡ ይህ ማለት አስቸኳዩ ጉዳይ ችግኝ ማግኘት ነው፡፡ ሲሆን ሲሆን ከቅርብ ቦታ፡፡ እኛና ኑርሁሴን አንድ ሃሳብ መጣልን፡፡ ይኸውም በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን የመጀመሩን አስፈላጊነትና

በአካባቢው ችግኝ አዘጋጅቶ ማቅረብ ከተቻለ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚያ ባሻገር የይቻላል መንፈስ ይፈጥርልናል፡፡ በዚሁም ደረጃ ሆኖ ክንውኑ የፉክክር መንፈስ በመፍጠር ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን እርስ በርሳቸው እንዲወዳደሩ ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች እንዲሆኑ ፈለግን፡፡ ስለዚህም ሌሎች አንድ ወይም ሁለት ሰዎች እንዲሳተፉ እላይ ከተጠቀሱት ውስጥ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ሶስቱን ወይም አራቱን የሚያሟሉ ፍለጋ ተጀምሮ ከተለያዩ ቦታዎች የሚከተሉት ሶስቱ ለመጀመሪያ ሙከራ ተመረጡ፡፡ እነሱም፡-

1. አርብቶአደር መሓመድ ከዲር ሽሪፍ - ከፍሾ ቀበሌ
2. አርብቶአደር ከዲር ሳሊሕ ጁሃር - ከዋሕዲስ ቀበሌ
3. አቶ ሑሴን መሓመድ ጋዓስ - ከፈረስ ደገ/ ኮነባ ቀበሌ

በኛ በኩል በከፊል አርብቶአደር መሓመድ ከዲር ሽሪፍ ላይ ከፍተኛ ፍላጎት እና መነሳሳት ስላስተዋልን ትልቅ ተስፋ ሰንቀን ለመጀመር ተነሳሳን፡፡ በፕሮጀክቱ በኩል ለነዚህ ከፍተኛ ተነሳሽነት ያሳዩ ግንባር ቀደም የልማት አርበኞች የተወሰኑ ቁሳቁሶች ማቅረብ እና ስልጠና መስጠት ከባድ አልነበረም፡፡

### 7.3.3. የስልጠናው ሂደት

**የካቲት 14፣ 2011 ዓ.ም**

ተሳታፊዎች ከኮነባ ከተማ ተነስተው መቐለ እንደደረሱ በወ/ሮ ሳራ ምስግና እና በአቶ አረፋይነ አስመላሽ (የዘላቂ ልማት መካነ ጥናት ሰራተኞች) የችግኝ ጣብያ አመሰራረት እና አያያዝ እንዲሁም የችግኝ አፈላል እና አያያዝ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በመቐለ የዘላቂ ልማት መካነ ጥናት ቢሮ ውስጥ የንድፈ ሃሳብ ስልጠና ወሰዱ፡፡

**የካቲት 15፣ 2011 ዓ.ም**

ውቅሮ ከተማ የሚገኘው ነባር የችግኝ ጣብያ ላይ በመሄድ በአቶ ካሕሳይ ባርያብሩክ እና አቶ ሐሽ (የክልተ አውላዕሎ ወረዳ ባለሙያዎች) አማካይነት ለችግኝ የሚሆን ዘር አመራረጥ፣ የአፈር ምጥጥን፣ የችግኝ ማፍያ መደብ አዘገጃጀት፣ የችግኝ አፈላል እና አያያዝ፣ ወዘተ የንድፈ-ሃሳብና የተግባር (ሙያዊ) ስልጠና ወሰዱ፡፡

## የካቲት 16፣ 2011 ዓ.ም

ውቅሮ ከተማ ውስጥ የበርካታ አመታት ልምድ ባለውና በግሉ የተለያዩ ችግኞችን የሚያዘጋጅ አርሶአደር ገ/ጅወርግስ ሓለፎም በተባለ ሰው አማካይነት ስለ ችግኝ ዝግጅት፣ ስለችግኝ መስሪያ መሳርያዎች አያያዝ እና የቋሚ አትክልት ችግኝ ማዳቀል የተግባር ስልጠና ሰለጠኑ፡፡ በማስቀጠልም (ከሰዓት በኋላ) ምን ያህል ግንዛቤ መጨበጥ እንደቻሉ ለመመዘን የተግባር ፈተና ተሰጣቸው፡፡ ውጤቱም እንደሚከተለው ነበር፡፡

- ሁሉም ሰልጣኞች በችግኝ ዝግጅት ጊዜ የሚያስፈልጉትን መሳርያዎችና ግብአቶች ዝርዝር (የችግኝ አፈር ለመቀየጥ የሚያስፈልጉ እንደ ለም አፈር፣ ፍግ/ኮምፖስት እና አሸዋ፣ እንዲሁም ለመደብ የሚሆን ቦታ መረጣ፣ ለችግኝ የሚሆን አፈር የሚጠቀጠቅበት ፕላስቲክ፣ ወዘተ) በአግባቡ ከመረዳት አኳያ ተገቢውን ግንዛቤ ጨብጠዋል፡፡
- ሁሉም ሰልጣኞች ለችግኝ ማዳቀል የሚያስፈልጉ መሳርያዎች በተለይ መቀስ፣ ሰንጢ፣ ለማፅጃ የሚሆን አልኮል እና ጥጥ፣ በመክተቢያ ጊዜ የሚያስፈልገውን የመጠቅለያ ላስቲክ እንደሚያስፈልጉ በአግባቡ ዘርዝረዋል፡፡

- ሁሉም ሰልጣኞች በማዳቀል ጊዜ የማዳቀያ መሳርያዎች እንዴት እንደሚያዝ በተገቢው መንገድ አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም በሚያዳቅሉበት ወቅት የእነዚህን መሳርያዎች አጠቃቀም እና አያያዝ እንዴት መሆን እንዳለበት ደረጃ በደረጃ ከማሳየትም አልፈው እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት የአቮካዶ ችግኝ በተግባር በማዳቀል አስመስክረዋል፡፡



ምስል 21፡- የችግኝ አፈላል ሰልጣኞች በሻይ እረፍት

በመሆኑም ሰልጣኞቹ ስለጠናውን በአግባቡ መከታተላቸውንና እንዴት እንደሚሰሩ በተግባር ስላሳዩ፤ እንዲሁም የስልጠናውን ዓለማ ከግብ ለመድረስና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲሰሩ ለእያንዳንዳቸው የማዳቀያ መቀስ፣ ሰንጢ፣ አልኮል ከነጥጡ እንዲሁም የውሃ ማጠጫ ባልዲ በስጦታ መልክ ተበርክቶላቸዋል፡፡

## 7.3.4. አሁን ያለበት ደረጃ

በ2011 በዝግጅት ነበር ያለፈው፡፡ ሆኖም በ2012 ዓ.ም የተደረገው ሙከራ ውጤቱ እስከ 1000 የተለያዩ ችግኞች ተዘጋጅቷል፡፡ በመስከረም 2013 ዓ.ም መጀመሪያ ሲቃኝ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች መታየት ጀምሯል፡፡ ይህ ማለት

- አብደላ ሩፋ (ከዋህዲስ)፡- ዘይቱን (500)፣ ቆንጥር (20)
- ሓጂታ መይረም (ከዋህዲስ)፡- ፓፓያ (50)፣ ዘይቱን (70)
- ሁሴን ዓሊ ሶኮሌ (ጋሓር/ከዋህዲስ)፡- ኮምጣጤ ብርቱኳን (10)፣ ፓፓያ (30)
- ሑሴን ሑመድ ሩፋ (ከበልበል)፡- ሎሚ (50)፣ ፓፓያ (200)፣ ቆንጥር (50)
- ይህ ጅማሮ ወደ ተመረጡ የችግኝ አይነቶች በጥራት ማዘጋጀት እና የገበያ ትስስር በመስራት ማብቃት የቀጣይ ስራ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በግለሰብ መዘጋጀት ከጀመረ በየዓመቱ የሚመደበው የመንግስት እና የአጋር አካላት በጀት በማስቀረት ዘላቂነቱ ያረጋግጣል፡፡ ቢሆንም የተለያዩ አካላት እና ህብረተሰቡ ከነሱ እንዲገዛ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡



ምስል 22፡- በአብደላ ሩፋ የተዘጋጀ ዘይቱን ችግኝ

## 7.3.5. የግዢ የችግኝ አቅርቦት ማስቀጠል

### 7.3.5.1 በ2011 ክረምት መዳረሻ የነበረ የችግኝ አቅርቦት

በ2011 ክረምት ታቅዶ የነበረው የችግኝ አቅርቦት በይዘንባል ተስፋ ብቻ በክረምት ዝናብ ላይ የተመረኮዘ ነበር፡፡ ይሁንና የክረምት ዝናብ ስላልነበረ የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህፀተ ዝናብ ኮሌጅ ተግዳሮቶቹን ለማቃለል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ካበረከታቸው ድጋፎች መካከል ለመጥቀስ ያክል፡- 985 የቋሚ አትክልት ችግኝ ገዝቷል፡፡ ህብረተሰቡ አዋጥቶ ተወካዩን ወደ ቆላ ተንቤን በመላክ 140 የብርትኳን ችግኞችን እንዲገዛ የማሳለጥ ሚናውን በአግባቡ ተወጥቷል፡፡

የምርጥ ተሞክሮ ማህበር በበኩሉ የመጓጓዣ አገልግሎት ከማቅረቡ ባሻገር 750 የተለያዩ የቋሚ አትክልት ችግኞች ከሃይቅመስሃል፣ ከተምቤን እና ከውቅሮ በመግዛት አቅርቧል። ሰንጠረዥ 1 ይመልከቱ።

### 7.3.5.2 በ2012 ክረምት የነበረ የችግኝ አቅርቦት

ከሰመራ ዩኒቨርስቲ ጋር የተገናኘነው በአቶ አብዱሰላም ሲሆን ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር እና ከምክትል ፕረዚደንቱ ከዶ/ር አብዱሰላም ከድር ጋር በስልክ ተገናኝተን ቀጠሮ ያዝን ከዚያ ወደ ሰመራ ተጉዤ ገለፃ አደረግኩላቸው። ከዚያ በኮነባ አብረን እንድንጎበኝ ተደረገ በተለይ ዋህዲስ ላይ የተፈጥሮ ምንጮች ጉብኝት አደረግን። ቀጥሎ በኮነባ በተደረገው የእውቅና ቀን በድጋሚ ተገናኝተን ጉብኝት አደረጉ። ከዚያ በኋላ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ባደረግነው በጋራ የመስራት ስምምነት መሰረት በመጀመሪያ 1,650 ቀጥሎ 3,900 የተለያዩ ችግኞችን ለወረዳው በእገዛ መልክ አስረክበው ለተጠቃሚዎች እንዲከፋል ተደርጓል። (ለተሻለ ሰንጠረዥ 2ን ይመልከቱ።)

### 7.3.5.3 የችግኝ ጣብያው እናት ዛፎች እንዳይደርቁ የተደረገ ሙከራ

ከላይ የተደረጉ እገዛዎችና ጥረቶች እንዳሉ ሆነው፣ ችግኙ ዝናብ በሌለበት መትከል ስላልተቻለ ከወረዳው መስተዳድር እና አርብቶአደር ፅ/ቤት ጋር በመመካከር የውሃ አቅርቦት ባለው የተመረጠ ቦታ ቆይቶ በነሃሴ መጨረሻ ላይ ችግኞቹን (የቡና፣ ብርቱኳን፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ወዘተ) መትከል ተችሏል። በችግኝ ጣብያው ቦታ ላይ በውሃ ማቆርያ ቅርፅ በተሰራ ቦታ ላይ በቆሎ ለመዝራት የተቻለ ሲሆን በእርከን መልክ የተሰራው ቦታ ላይ ደግሞ ለመኖነት የሚውሉ የተለያዩ የሳር ዓይነቶች ተተክለዋል።

እንዲያም ሆኖ አሁንም የውሃ ችግር እንዳለ ነው፡፡ ለጊዜው አንድ መጠኑ 5*3*7 ሜትር የሆነ የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ውሃ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ ቢሆንም ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ስለዚህም ከዚሁ የውሃ ማጠራቀሚያ ጋራ የሚኖረው ልዩነትም ማየት እንዲቻል እርከኑን ከፍ አድርጎ ስርጉድ መደብ በማዘጋጀት የግማሽ ጨረቃ ቅርፅ ባለው የግንባታ አሰራር መንገድ ሌላ ተጨማሪ የውሃ ማቆርያ እንዲዘጋጅ በመመካከር ስምምነት ላይ ስለተደረሰ በተባለው መሰረት ተሰርቶ እርጥበት መያዝ ችሏል፡፡



ስእል 23፡- ችግኝ ጣብያ ላይ የተሰራው የውሃ ማቆርያ ጉድጓድ

## 7.3.6. ያልታሰብ እና ያልተገመተ መልካም ነገር

አንድ ወቅት አቶ ኑርሁሴን ከማል ከአቶ መሃመድኑር (አዲሱ የአርብቶ አደር ፅ/ቤት ሃላፊ) ጋር በመሆን ወደ በራህሌ ወረዳ ሄደው ነበር፡፡ አብረው የተጓዙበት ዋናው ምክንያትም አቶ መሃመድኑር ከኮነባ ወረዳ የብርቱኳን ችግኝ

ገዝቶ ቤተሰቦቹ ቦታ ላይ ተክሎ ስለነበረ ነው፡፡ አቶ መሓመድኑር ወደ ቦታው እየተመላለሰ ሲከታተል ብርቱኳኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ ተመልክቷል፡፡ ቢሆንም ኮነባ ወረዳ ላይ ክትትል እና ገረዛ እየተደረገ ስለተመለከተ ነበር ኑርሁሴንን እንዲያይለትና እንዲገርዝለት የጋበዘው፡፡

ቢሆንም መሃመድኑር ችግኙን ከመትከሉ በቀር ማን እንደሚንከባከበው አልተናገረም ነበር፡፡ እንደደረሱ የሆነው ግን አስገራሚ ነበር፡፡ ደርሰው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ እናት እና ልጅ ብርቱኳኑ ጥሩ እንደሆነላቸው በኩራት ተናገሩ፡፡ ሆኖም ግን እነሱ አሁን ስለታሰበው የችግኝ ገረዛ ምንም ቅድመ መረጃ አልነበራቸውም፡፡ ባለሙያ መጥቶ ያደንቅልናል ብለው ሲገምቱ ኑርሁሴን አላስፈላጊ ቅርንጫፎቹን መግረዝ ሲጀምር እናት ተናደደች፤ ልጇም አለቀሰ፡፡ እንደተቆረጠባቸው እንጂ ገረዛው አስፈላጊ እንደሆነ አላወቁም ነበር፡፡

ኑርሁሴን ይህንን "የልጆቹና እናታቸው ሁኔታ አይቼ ብደነግጥም ችግኙን ይሄን ያህል እንደሚወዱት እና እንደሚንከባከቡት አልገመትኩም ነበር ቢሆንም ግን ይሄን በማወቄ ደስ ብሎኛል" በማለት ነበር ክስተቱን የገለፀው፡፡ ምክንያቱም በኮነባ ወረዳ የተለመደው ጉብኝት እና ገረዛ ሲደረግ ተሳታፊ የነበሩት አባወራዎቹ/ ባሎቻቸው ብቻ ስለነበሩ ሴቶቹና ልጆቻቸው በቋሚ አትክልት ልማት ላይ ያላቸው ተሳትፎ እና ስሜት አይታወቅም ነበር፡፡

በስተመጨረሻው ኑርሁሴን በእለቱ ስላጋጠመው ክስተት እንዲህ በማለት ትዝብቱ አስፍሯል፡-

*አሁን የዚህ የቋሚ አትክልት ልማት ስራ ዘላቂነት ገባኝ፡፡ ምክንያቱም ወንዶች የትም ቢጓዙ እንኳን ሌላው የቤተሰብ አባል አለ፡፡ ቢሆንም ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ፡፡ እነሱም፡-*

1. *ለሴቶች እና ልጆቻቸው ልዩ ስልጠና ያስፈልጋል፡፡ ስልጠናው ከሀ-ፐ ማለትም ከመሬት ዝግጅት፣ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ አተካከል፣ ክትትል (ውሃ ማጠጣት፣ ገረዛ፣ ተባይ መከላከል፣ ወዘተ) ናቸው፡፡ ስልጠናው ቀለል ባለና ስእላዊ በሆነ መልኩ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡ ለዚሁ ይረዳ ዘንድ ትንሽ ስእላዊ ፖስተር ቢዘጋጅ የሚል ሃሳብ አለው፡፡*
2. *ለሴቶች ስልጠና ባህሉ በተከተለ መልኩ መሆን ስላለበት ስልጠናው በሴት አሰልጣኞች ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም እማወራዎች ባል ሳይኖር ሌላ ወንድ ማነጋገር ባህሉ እና ልማዱ ስለማይፈቅድላቸው ነው፡፡*

## 7.4. ለሩሕ ተፋሰስ ስራ የተደረገ ቅድመ-ዝግጅት

### 7.4.1. በአካባቢው ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል

በኮነባ ወረዳ ውስጥ የተፋሰስ ስራ እንዲሰራ የሚያስገድዱ አራት ቁልፍ ችግሮች አሉ፡፡ እነሱም፡-

1. በወረዳው ከነበሩት የተፈጥሮ የውሃ ምንጮች ውስጥ አብዛኞቹ በመድረቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ አሁን ካሉት ውስጥ የዋሕዲስ ቀበሌ ሶስቱ ምንጮች ሲሆኑ የውሃ መጠናቸው እጅግ ስለቀነሰ የሚሰጡት አገልግሎትም እንዲሁ አጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ቀደም ባሉ ግዜያት ለመስኖም ሳይቀር እየተጠቀሙ እንደነበር ነው፤ አሁን ግን ለሰው እና ለእንስሳት የመጠጥ ግልጋሎት እንኳን ማሟላት ተስኗቸዋል፡፡
2. ከደጋው የሚዋሰነው አካባቢ በአብዛኛው ሳሩ እና ቅጠሉ የተበላ በመሆኑ ዝናብ ሲዘንብ የጎርፉ ፍጥነት ከሚገመተው በላይ ሆኗል፡፡ ይባስ ብሎ በእሩሕ ቀበሌ ያለው ቦረቦር ጥልቀቱ፣ ስፋቱ እና ርዝመቱ ከግዜ

ወደ ግዜ እጅግ እየጨመረ በመምጣቱ ተስፋ አስቆራጭ እስከመሆን ደርሷል፡፡

3. በአሁኑ ሰዓት በኮነባ ወረዳ ውስጥ ሳር ማግኘት ከባድ ነው፡፡ በግል ከታጠሩት የእርሻ ቦታዎች ውጪ ሳር በምድሩ አይታይም፡፡ ለዚህም ይመስላል ከፍየል፣ ግመል እና አህያ ውጪ የቀንድ ከብቶች ማየት ብርቅ የሆነው፡፡ ሳር ለማብቀል ሲባል መሬታቸውን ደህና አድርገው ያጥራሉ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ወደ ታጠረው ቦታቸው የጎርፍ መቀልበሻ ሰርተው ከደጋው የሚመጣውን የጎርፍ ውሃ ወደ እርሻቸው ያስገባሉ፡፡ ይህም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአካባቢው ህብረተሰብ ነባር እውቀት/ክህሎት ነው፡፡

4. ወረዳው በሙሉ ወይም በከፊል በጎርፍ የተጠቃ ነው፡፡ ሁልጊዜ ነዋሪው እና እንስሳቱ በደራሽ ጎርፍ እንደተጠቃ ነው፡፡







ምስል 24፡- የእሩሕ ተፋሰስ የአፈር መሸርሸር አደጋ

ወረዳው የምግብ ዋስትና ችግር ስላለበት የሴፍት ኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ነው፡፡ የወረዳው መስተዳድርና ማህበረሰብም 'በሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ስራ አማካይነት የዋሕዲስ ምንጭ ማጎልበት እና የእሩሕ ተፋሰስ ስራ እንሰራለን' የሚል አቋም ይዘው ስለተነሱ የፔለም ኢትዮጵያ ከምርጥ ተሞክሮ ማህበር ጋር በመሆን ለቅድመ ዝግጅቶች አጋዥ የሆኑ የሚከተሉትን ተግበራት አከናውኗል፡፡ እነሱም፡-

## 7.4.2. ከአብረሃ ወአፅበሃ ወደ ኮነባ የተደረገ የአባ ሓዊ ጉብኝት እና የሰጠው አስተያየት

አባ ሓዊ የገብረሚካኤል ግደይ ቅፅል ስም ነው፡፡ አባ ሓዊ ለረጅም ጊዜ (ከ30 ዓመታት በላይ) የአብርሃ ወአፅበሃ ቀበሌ ሊቀ-መንበር የነበረና የተለያዩ የልማት ስራዎችን በመምራት እና በመተግበር በክልሉ የታወቀ የግብርና ባለሙያና በተሰጥኦ የአርሶአደር መሃንዲስ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ጡረታ ቢወጣም የካበተ የተግባር ልምድ ስላለው የተለያዩ ድርጅቶች

በአማካሪነት እና ባለሙያነት እንዲያገለግላቸው ለአጭር ጊዜ ይቀጥሩታል፡፡

በተመሳሳይ አንድ ጊዜ ወደ ዋሕዲስ ምንጮች እና አንዴ ደግሞ ወደ እሩሕ ተፋሰስ በመጓዝና ከህዝቡ ጋር ጉብኝት በማድረግ ምክሩን ለግሶ ነበር፡፡ በምንጮቹ አካባቢ የእፅዋት ሽፋን እየሳሳ ከሄደ እና የቤት እንስሳትን ቀጥታ በምንጩ ላይ ውሃ ማጠጣት ለምንጩ ዋና ችግር መሆኑን ጠቁሟል፡፡ በማከልም “ምንጩን ለማጎልበት እና የእፅዋት ሽፋንን ለማሻሻል የተፋሰስ ስራ እና ተፋሰሱ ከከብት ንክኪ ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል” የሚል ገንቢ የመፍትሄ ሃሳብ ያዘለ አስተያየት ሰንዝሯል፡፡

ህብረተሰቡም ከፔለም ኢትዮጵያ እና ምርጥ ተሞክሮ ማህበር ጋር ሆነው ለመስራት እንደሚፈልጉ ሃሳብ አቀረቡ፡፡ ይሁን እንጂ እንዚህ ተቋማት የልምድ ልውውጥ፣ ባለሙያ/አማካሪ ማቅረብ እና የመሳሰሉት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ወጪ መሸፈን እንደማይቻላቸው አብራሩላቸው፡፡ እነሱም ይህን የልማት አጀንዳ ሌላ የበጀት አማራጭ እንዳላቸው ማለትም በሴፍትኔት ፕሮግራም አማካይነት በጀት አስይዘው ሊሰሩት እንደሚችሉ ቃል ገቡ፡፡ ስለዚህ ከዚህ በመቀጠል የተሳካ ሰራ ለመስራት ከተፈለገ የህብረትሰቡ ግንዛቤ ወሳኝ ነው፡ ስለዚህ በስራው የሚሳተፉ አካላት ሄደው ተመሳሳይ ስራ እንዲያዩ ሃሳብ ቀረበ፡፡

## 7.4.3. ከዋሕዲስ እና ከእሩሕ የተውጣጡ ፎርማኖች የልምድ ልውውጥ ክንውን

ከላይ በቀረበው ሃሳብ መሰረት የልምድ ልውውጡን መርሃ-ግብር የሚያስተባብሩ ከሁለቱ ቀበሌዎች እና ከወረዳው ግብርና ሰራተኞች መካከል ስምንት (8) ሰዎች ተመረጡ፡፡ እነዚህም ከዋሕዲስ እና እሩሕ ከእያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት

ፎርማኖች፣ እንዲሁም ከወረዳው ሁለት ባለሙያዎች ተመረጡ፡፡

ጉብኝቱም እንደሚከተለው ተካሄደ፡-

### *7.4.3.1. አብዓላ ወረዳ የተደረገ ጉብኝት፡-*

ጉብኝቱ በአብዓላ ወረዳ፣ በዓሰንጎላ ቀበሌ ነበር የተካሄደው፡፡ እዚህ አካባቢ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የውሃ እና የግጦሽ አቅርቦት እጥረት አለባቸው፡፡ ወጣቶች እንደሚሉት እንስሳቶቻቸውን ውሃ ለማጠጣት ደርሶ መልስ እስከ አንድ ቀን ተኩል ድረስ መጓዝ ግድ ይል ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር ምንም እንኳን በመንግስት እገዛ ለሰው የመጠጥ ውሃ ግልጋሎት የሚሰጥ የውሃ ጉድጓድ ተገንብቶ የነበረ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎቱ የመድረቅና የመበላሸት እድል ስለሚያጋጥመው የሚፈለገው ያህል አይደለም፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል የውሃ ጉዳይ አንዱና ዋንኛው ነው፡፡



ስእል 25፡- በዓሰንጎላ የተገነባው የውሃ ማቆርያ

በአሁኑ ወቅት ይህን ችግር በተወሰነ መልኩ ለማቃለል የሚያግዙ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው፡፡ በስፍራው የውሃ ማቆር ተግባራት በመከናወናቸውና የአከባቢው ህብረተሰቡ የውሃ አቅርቦት በማግኘቱ ወደ ውሃው አካባቢ መሰባሰብ ጀምሯል፡፡ (ስእል 25ን ይመልከቱ)፡፡ እንዲህ አይነቱ ችግርን የሚቀርፍ ተግባር ማከናወን እንደሚቻል በማወቃቸውና ግንዛቤ ስላሳደሩም ተደስተዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የጉልበት ስራ አስተዋፅኦ በማድረግ የውሃው እና የእርጥበት ማቆርያ እንዲሁም የተተከሉ እፅዋቶችን በመንከባከብ ረገድ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡

### *7.4.3.2. ቃልአሚን ቀበሌ አፅቢ ወንበርታ ወረዳ የተደረገ የጎርፍ አልባ ተፋሰስ ጉብኝት፡-*

የካቲት 2010 ዓ.ም. በቃል አሚን ቀበሌ ከሚገኘው 51 ሄክታር ጎርፍ አልባ ተፋሰስ መካከል በ19.5 ሄክታር ላይ የውሃ እና የአፈር ጥበቃ ስራ ተጀመረ፡፡ በመቀጠል 31.5 ሄክታር ላይ የአፈርና ውሃ እቀባውን/ጥበቃውን በማስፋፋት ክንውኑ በ2011 ዓ.ም. ተጠናቀቀ፡፡ በዚህ ክንውን የተገኘው አመርቂ ውጤት ደግሞ እጅግ ማራኪና አስተማሪ ሆኖ ተገኘ፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ፡-

1. ከተተከለው የወይራ ችግኝ ውስጥ 98 ከመቶ መፅደቁ ተረጋግጧል፡፡
2. በተፋሰሱ ውስጥ ያለው የሳር ቅጠሉ አበቃቀል ሲቃኝ አጅግ አድናቆት የሚቸረው ሲሆን በአንድ እና ሁለት ዓመት ጊዜ እዚህ ደረጃ ይደርሳል ብሎ መገመት ያዳግታል፡፡ (በምስል 26 ያለውን ይመልከቱ)፡፡



ምስል 26፡- በአጭር ጊዜ ያገገመው የቃላሚን ተፋሰስ ሲጎበኝ

3. በመከለሉ ብቻ በአጭር ጊዜ ጠፍተው የነበሩ ነባር የእፅዋት ዝርያዎች በቀላሉ ማገገምና ለማቆጠጥቆጥ ችለዋል፡፡ (ምስል 26ን ይመልከቱ)፡፡

### *7.4.3.3. በአብርሃ ወአፅበሃ ቀበሌ ክልተ አውላዕሎ የተቀናጀ ተፋሰስ የተደረገ ጉብኝት*

በአብርሃ ወአፅብሃ ቀበሌ የተከናወነው ጉብኝት በሚከተለው አኳኋን የተካሄደ ነበር፡-

1. በቀበሌው የሚገኙትን የተቀናጀ የተፋሰስ እና የውሃ ማቆር ስራዎችን የጎበኙ ሲሆን ከዚሁ በተያያዘ የተለያዩ የቸክ ዳም አሰራርንና ካጠራቀሙት የውሃ መጠን በመነሳትም ውሃ የመያዝ ዓቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ ለመገንዘብ ችለዋል፡፡
2. በአጠቃላይ ሲታይ የተፈጥሮ ሃብት መከለል (ከሰውና እንስሳት ንክኪ በጥብቅ የደን ይዞታ አግባብ) ከመትከል የተሻለ ተፈጥሮ ሃብት እንዲያገግም እንደሚረዳ ልዩ ትምህርት ቀስመውበታል፡፡

3. በአባ ሓዊ ቤት ደግሞ በትንሽ መሬት የተሻለ ምርት እንደሚገኝ ለመታዘብ ችለዋል፡፡ በተጨማሪም፣
4. በአባ ሓዊ ቤት በአንድ ቤት ውስጥ ሶስት የውሃ አማራጮች እንዴት መያዝ እንደሚቻል ለመቃኘት ችለዋል፡፡



ምስል 27፡- የአባ ሃዊ ስራዎች በከፊል

### *7.4.3.4. ለፕሮጀክት የታሰበው ቦታ ላይ የተደረገ ጉብኝት*

የእሩሕን ጉብኝት ለማካሄድ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት የእሩሕ ተፋሰስ ምን እንደሚመስል እና እንዴት ሊሰራ እንደሚችል ከአባ ሓዊ ጋር አብሮ ለመወያየት ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ነበር ያልጠበቅነውን ሰፊ፣ ረጅም እና ጥልቅ ቦረቦር ያለውን መሬት ለመመልከት የቻልነው፡፡ በመጀመርያ አባ ሓዊ ይህንን ካስተዋለ በኂላ በአጥር በተከለለው እያንዳንዱ ከፊል አርብቶአደር ቦታ ላይ ተፋሰሱን በመስራት በቀላሉ ማስጀመር እንደሚቻል አሳሰበን፡፡ ለዚህ ቦታ ዋናው መፍትሄ የውሃ ማቆርያ እና ማስረግያ (Percolletion pond) ተግባራት ማከናወን እንደሆነና ይህም በሰብልም ሆነ በሳር ልማት ረገድ በአጭር ጊዜ የተሻለ ውጤት ሊያሳይ እንደሚችል መግባባት ላይ ደረስን፡፡

በዚያን ሃሩራማና ደረቃማ አከባቢ አለፍ አለፍ እያሉ ግቢያቸውን በሎሚ፣ ብርትኳን፣ ዘይትሁን፣ ትርንጎ ቋሚ ተክሎች እስትንፋስ የዘሩ መኖርያ ቤቶችን ለማስተዋል ችለናል፡፡ በዚህ ሃሩር እና ዝናብ አልባ ብቻ ሳይሆን፣ የአንገተ ረጅሙ ግመል ጥቃትንም አልበገር የሚል ሰው በተለይም እናቶች መኖራቸውን ስታይ የሰውልጅ ጥንካሬን ከማድነቅ ባሻገር ተስፋ ሰጪ ሁኔታ እንዳለ ጭምርም ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ አባ ሓዊ እዚህ ቦታ የተፋሰስ እና የጋብዮን ክትር ስራዎች ከተከናወኑ በአጭር ጊዜ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል በሰጠን የመፍትሄ ሃሳብ ተስፋችን የበለጠ ለመለመ፡፡

### *7.4.3.5. በልምድ ልውውጥ መርሀ-ግብር የኮነባ ወረዳ ካቢኔ አባላት ተሳትፎ*

በፕሮጀክቱ አስተባባሪነት የሚካሄደው የልማት መርሃ-ግብር ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ‘አለቆችም ይሄን የልማት ስራ ይጎብኙት፤ ግንዛቤም ቢወስዱ ይመረጣል‘ በማለት ስምንት የሁለት ቀበሌ ተወካዮች እና ሁለት ባለሙያዎች በሰጡት ማሳሰብያ መሰረት ስድስት የወረዳ ካቢኔ አባላት ተለይተው ለአንድ ቀን ጉብኝት ወደ ትግራይ ሄደው እንዲጎበኙ መግባባት ላይ ስለተደረሰ ቃልአሚንን እና አብርሃ ወአፅበሃን እንዲጎበኙ ተደረገ፡፡ የካቢኔ አባላቱ በጉብኝቱ እጅግ ከመርካታቸው የተነሳም እንዴት እናስተግብረው በሚለው ለመወያየት በቃን፡፡

አባ ሓዊም በአማካሪነት የውይይቱ ተሳታፊ ነበር፡፡ የወረዳው ካቢኔ በተለይ የወረዳው አስተዳዳሪ በጣም ጓጉተው ነበር፡፡ በተጨማሪም የአፅቢ ወንበርታ ወረዳ ግብር ፅ/ቤት ሃላፊ አቶ ሃይላይ ገብረ ቃልአሚንን ካስጎበኘን በኋላ ባዘጋጁልን የምሳ ግብዣ ላይ ውይይት ስናደርግ ጎብኚዎቹ የካቢኔ አባላት የሙያ እገዛ እንዲደረግላቸው ጠይቀው ነበር፡፡ አቶ ሃይላይም

በወረዳው አስተዳደር ስም ከሙያተኛ እስከ ቁሳቁስ ሁሉንም ለመደገፍ ዝግጁ እንደሆኑ ቃል ገብተውላቸዋል፡፡ የጉብኝቱ መርሃ ግብርም በዚሁ ተጠናቀቀ፡፡

## 7.5. የወረዳው ካቢኔ አባላት ስለተፋሰስ ስራው ያስተላለፉት ውሳኔ

የወረዳው ካቢኔ አባላት ሌላ ቦታ ላይ ጎብኝተው ከተመለሱ በኋላ እኛ ራሳችን እንዴት እንስራው በሚል ጉዳይ ላይ ተወያዩ፡፡ ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም ነው ነገሩ፡፡ ፔልም ኢትዮጵያም ምርጥ ተሞክሮ ማህበርም በነሱ አቅም እንደማይሞከር ተናገሩ፡፡ ሆኖም ወረዳው እገዛ ካገኘ በምግብ ዋስትና ስራ ብዙ የመራመድ እድል እንዳለው ተስፋ ማድረግ ጀመረ፡፡

አንድ ቀን ከቢሮ ሃላፊው ከአቶ ዓሊ ሑሴን ወይሳ ለመገናኘት ቻልን እና ያለው የፕሮጀክት ስራ ከገለፅኩላቸው በኋላ በመደሰት ምን ችግር አለ? ምን እናግዛችሁ? አሉኝ፡፡ እኔም የእሩሕ ተፋሰስ ለመስራት ችግር ጠቅሼ በማተሪያል እንዲግዙን ጠየቅኳቸው፡፡ በደስታ ማተሪያል ለማፈላለግ እንደሚያግዙን ተስፋ ሰጡን፡፡

በ2013 መጀመሪያ ላይ ከቢሮ ሃላፊው እና ከወረዳው አካላት አብዓላ ተገናኝተን ስራ ተከፋፈልን፡፡ 1. ጋብዮን የክልሉ ቢሮ፣ 2. ሲሚንቶ እና ልምድ ያለው አማካሪ ፔለም ኢትዮጵያ/ ምርጥ ተሞክሮ ማህበር፣ እንዲሁም የተቀረው ወረዳው እንዲሸፍን ተስማምተን ተለያየን፡፡

# 8 እውቅናና ሽልማት

በህብረተሰቡ አስተሳሰብ መሰረት እንደመሪ ቃል እያንዳንዱ የልማት አርበኛ ይጠቀስ! የፊታውራሪነት ስራቸው ይዘገብ፡፡ ይሸለም፡፡ ብለው ሃሳብ አቀረቡ፡፡



ምስል 28፡- የሽልማት ስነ-ስርዓት በከፊል

የሽልማት ስነ-ስርዓቱ የተዘጋጀው አመርቂ ስራን ለሰራ ሰው ወይም አካል ትልቅ ማበረታቻና ይበልጥ እንዲተጋ ሞራሉን እንዲገነባ ለማድረግ ሲሆን በተለይም ከእጩዎቹ አመራረጥ ጀምሮ በአግባቡ የተከናወነ የሽልማት ስነ-ስርዓት ሲሆን ሁሉንም ሰው የሰራውን ስራ እውቅና በመስጠቱ የበለጠ እንዲተጋና ሌላውም በቀና የቅናት መንፈስ ሞራሉ እንዲነሳሳ ለማድረግና በተጠቃሚዎች መካከል የውድድር መንፈሰ ለመፍጠር ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ የሽልማቱ ሂደትም በወረዳው ውስጥ ያሉ የልማት ተሳታፊዎች በሶስት ምድቦች በመክፈል የተከናወነ ሲሆን በጠቅላላው ለ15 ሰዎች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ እነዚህም፡-

- አንደኛ በመስኖ የሚጠቀሙ ከፊል አርብቶአደሮች፡- በዚህ ምድብ ምርጥና አስተማሪ የሚባሉ ጥምር እርሻ አራት የልማት አርበኞች ለሽልማቱ በቅተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ከበልበል ቀበሌ አካባቢ ናቸው፡፡
- ሁለተኛ በዝናብ ብቻ የሚጠቀሙ ከፊል አርብቶአደሮች፡- በዚህ ምድብ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ፣ ውሃን በማጠራቀም ብቻ የሚያለሙ ስድስት ከፊል አርብቶአደሮች ለሽልማቱ በቅተዋል፡፡
- ሶስተኛው ምድብ ከከተማ ነዋሪዎች፣ የካቢኔ አባላት እና የመንግስት ሰራተኞች ሚና ጉልህ ሚና ያበረከቱትን ያካተተ ነው፡፡ በዚህ ምድብ ለአምስት ሰዎች ሽልማት ተበርክቷል፡፡ እነዚህ የካቢኔ አባላት እና የመንግስት ሰራተኞች ለሽልማት የበቁትበት ምክንያትም በቢሮ ተሳትፎአቸው ሳይሆን በሚኖሩበት ቦታ፣ ግቢ፣ በእርሻ ቦታዎቻቸው፣ ወዘተ ላይ የሰሩት ስራ አመርቂነት ተገምግሞ አስተማሪነቱ ተመዝኖ ከታመነበት በኋላ ነው፡፡

የተሰጠው የሽልማት ዓይነት ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡፡ እነሱም ለገጠራማ ተሸላሚዎች የፀሃይ (ሶላር) መብራቶች ሲሆን ለከተማ ተሸላሚዎች ደግሞ የውሃ ማጣርያ ነው፡፡ በተጨማሪም ለሌሎች 15 ተከታይ ከፊል አርብቶአደሮች ልዩ ልዩ የእርሻ መሳሪያዎች (ዶማ፣ ማጭድ እና መጋፊያ) በሽልማት መልክ ተበርክቶላቸዋል፡፡ ከሽልማት ስነ-ስርዓት በኋላ ሶስት መርሃ ግብሮች ተካሂደው ነበር፡፡ እነሱም፡-

1. **ጉብኝት፡-** ተሳታፊዎች በቡድን ተከፍለው ወደ ተለያዩ ቦታዎች ለጉብኝት ሄደው ነበር፡፡ እነዚህም ወደ ዋህዲስ እና ፈረስ ደጌ ቀበሌዎች ተጉዘው፣ የቋሚ አትክልት

ችግኝ ጣብያ እና ከተማ ውስጥ የሚገኙ የተመረጡ ስራዎችን ጎብኝተዋል፡፡

2. **ከተሸላሚ ከፊል አርብቶ አደሮች ጋር ውይይት፡-** ከተሸላሚ አርብቶአደሮች ጋር የተደረገ ውይይት አጅግ አስደሳችና ማራኪ ነበር፡፡ ይኸውም ከፊል አርብቶአደሮቹ ጠባቂነት በማያስመጣ መልኩ የላቀ ፋይዳ ያለውን የልምድ ልውውጥ የስለጠና አግባብ መፈለጋቸውንና መምረጣቸውን ነው፡፡ ሰዉ ብር ስለተከፈለው ብቻ ምንም አይለወጥም፤ የልምድ ልውውጥ ግን ሰውን ይለውጣል በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

3. **የባለድርሻ አካላት ውይይት፡-** በዚህ የፕሮጀክት መርሃ-ግብር በባለድርሻነት የተለዩትና በውይይቱ የተሳተፉት፡- የግብርና ሚኒስቴርን፣ የአፋር ክልል የእንስሳት፣ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮንና፣ የወረዳው የእንስሳት፣ ግብርናና ገጠር ልማት ፅ/ቤትን በመወከል የተገኙ አካላት፤ እንዲሁም ከምርጥ ተሞክሮ ማህበር፣ ፔለም ኢትዮጵያ፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ (ፕሬዚደንቱ)፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲና የመሳሰሉ ተቋማትን ወክለው የተገኙ ናቸው፡፡ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀጣይ የፕሮጀክቱ መርሃ ግብር አብረው እንደሚሰሩ የጋራ ስምምነት የደረሱ ሲሆን ለዚህም የጋራ እቅድ እንዲዘጋጅ፣ የክልሉ ግብርናና አርብቶ አደር ደግሞ እንዲያስተባብር እና በተነደፈ የጊዜ ሰሌዳ ለባለድርሻ አካላቱ ጥሪ እያደረገ እንዲያሰባስብ ሃላፊነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ለዚህ መልካም ተግባሩም ዩኒቨርሲቲው ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሰው!

# 9 ማጠቃለያ እና አስተያየት

በኮነባ ወረዳ የታየው የልማት እመርታ በነዚህ ሁለትና ሶስት ዓመታት ብቻ የተመዘገበ መሆኑን ለማመን አዳጋች ቢሆንም በህብረተሰቡ፣ ባለሙያው እና የአካባቢው መስተዳደር ተሳትፎ እውን መሆን ችሏል፡፡ ክንውኖቹ ስኬታማ የሆኑበትም ሚስጥር ከሰባት ምክንያቶች የሚመነጩ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

- **አንደኛ፡-** የፕሮጀክቱ ዓላማ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ኑሮውን የሚመራ ሰው፣ ድህነቱን አምኖ ተቀበሎ የእለት ፍጆታ ከመርዳት ይልቅ ማንም ሰው ጠባቂነት በማያመጣ መልኩ ሰርቶ መለወጥ እንደሚችል ማሳመንና ተቀባይነት እንዲያገኝ ከማድረግ አኳያ የተመረጠው አካሄድ ነው፡፡ ይህም ማለት ገና ከውጥኑ እርዳታ ሊሰጥህ ነው በማለት የሚጀመር እገዛ የተረጅነት ስሜትን ማበረታታት ስለሆነ ከዚህ ይልቅ እገዛው ሰርቶ በሚለወጥበት ላይ ያተኮረ እንደሆነ መተማመን ላይ መድረስ ከቀዳሚዎቹ ሁሉ የቅድሚያ ስራ መሆን እንዳለበት ከጅምሩ አቋም መውሰድ ያስፈልጋል፡፡
- **ሁለተኛ፡-** ፕሮጀክቱ ሲጀመር ከእቅድ እስከ ተግባራቱ የአጋር ድርጅቶች፣ የህብረተሰቡ እና የመንግስት አካላት ተናበው መጀመራቸውና የስራው ተዋናዮች መሆናቸው ነው፡፡
- **ሶስተኛ፡-** ማንኛውም ስራ ሲጀመር ተጠቃሚው ማህበረሰብ አትኩሮቶቻቸው ተማክሎ በጋራ መንቀሳቀስ እንዲችሉ በተመሳሳይ ሁኔታ ዓይናቸው እንዲያይ በተግባር ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አካሄድ የሚካሄዱ የጉብኝት መርሃ-ግብሮችም በጎብኚዎቹ/ተጠቃሚዎቹ የመንፈስ ቅናትንና ተነሳሽነትን ይፈጥራል፡፡ የትግበራው

ስራ ጀማሪ የህብረተሰብ ክፍልም ምንም እንኳን በቁጥር አነስተኛ ቢሆንም ከዚሁ ክፍልም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ አባላት ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ በዚሁም አማካይነት እንዴት እንደሚጀምሩ ሳይሆን ሲሰሩት የነበረው ምን እንደጎደለ በቀላሉ መለየት ይቻላቸዋል፤ ለማስተካከልም ይቀላቸዋል፡፡ እግረ መንገዱም በሰሩት ስራ እውቅና ያገኙበታል ማለት ነው፡፡

- **አራተኛ፡-** ማናቸውንም የፕሮጅክቱ ተግባራት ከውጥናቸው ጀምሮ የፕሮጀክቱን ታማኝነት፣ ጠቃሚነትና ቀጣይነት በሚያረጋግጥ መልኩ ለህብረተሰብ የተወሰነም ቢሆን በአጭር ጊዜ ፈጣን ጥቅም ወይም የሚታይ ተስፋ ለተጠቃሚው በመስጠት የተቃኙ መሆን አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የልፋታቸው ውጤት ለማየት ብዙ መጠበቅ የለባቸውም፡፡
- **አምስተኛ፡-** ፈጣን ለውጥ ላመጡ ተጠቃሚዎችና ተዋናዮች ተከታታይ ጉብኝቶችን ከማመቻቸት ባለፈ እውቅናና ሽልማት በመስጠት የመንፈስ ውድድር እንዲፈጥሩ ያልተቆራረጠ ጥረት ከመደረጉ የተነሳ ነው፡፡
- **ስድስተኛ፡-** ባለሙያዎች ዘወትር ሊጎበኟቸው እንደማይችሉ የታወቀ ነው፡፡ በመሆኑም ክፍተቶቹ የሚሞሉበት የእርስ በርሳቸው የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም እንዲኖራቸው ማለማመድ ይገባል፡፡ በዚህ አማካይነት የእርሰበርስ ግንኙነት እና መማማር ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይህ አካሄድም ለፕሮጀክቱ ስኬታማነት ድርሻ አበርክቷል፡፡ ይሁንና ይህን መሰሉ አፈፃፀም በሚከናወንበት ወቅት በተከታታይ አንድ ሰው ላይ የጉብኝት ፕሮግራም

ላለማካሄድ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል በተለምዶ ጉብኝት የሱ ብቻ ይመስለዋል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ባለመጎብኘታቸው ይከፋቸዋል፡፡

- **ሰባተኛ፡-** ወደተቀረው የህበረተሰብ ክፍል ማስፋት በሚያስፈልግበት ወቅት በታታሪና ታማኝ አባል ጠቋሚነትና ምክክርነት አማካይነት ወደ ጎን (ወደ ሌላ ሰው) እንዲሰፋ ቢደረግ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም እራሱ እየመራው ወይም እያስተማረው ከመቀጠል አልፎ ለውድቀቱም ይሁን ለመሻሻሉ ሃላፊነት ይወስዳልና ነው፡፡

# 10 በኮነባ ወረዳ ዋና ዋና ቀጣይ የቤት ስራዎች

በኮነባ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች እና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ሀ. በአንድ በኩል ድርቅ በሌላ በኩል ደግሞ ጎርፍ በአካባቢው በሰፊው ይከሰታል፡፡ ለዚህ ችግር የጎርፍ መቀልበሻ በመስራት አሳታፊ የመስኖ እርሻ እንዲሰራ ቢደረግ ይመረጣል፡፡

ለ. የእንስሳት በሽታ እና የተፈጥሮ ተባይ በተለይ የአንበጣ መንጋ በየጊዜው ስለሚከሰት ሁሉ ጊዜ የመከላከል ዝግጅት ያስፈልጋል፡፡

ሐ. በአካባቢው የተሻለ የጥምር እርሻ ሙከራ በመኖሩ የችግኝ ፍላጎት ስለጨመረ የአቅርቦት እጥረት አለ፡፡ ስለዚህ በአካባቢው ጠባቂነት በማያስመጣ መልኩ የችግኝ አቅርቦት ማሻሻል ላይ እንዲሰራ፡፡

መ. ባህላዊ የስድ ግጦሽ የህብረተሰቡን ጥረት ላይ አስቸጋሪ ሆኗል ምክንያቱም ግመሎች በሌሊት እርሻ ያጠቃሉ፡፡ ስለዚህ በተለያየ መልኩ የአጥር ችግር መፍታት ወሳኝ ነው፡፡

ሠ. የአካባቢው ህብረተሰብ ዋነኛ ችግር አንዱ ነፋስ ነው፡፡ ነፋሱ የፓፓያ እና የሙዝ ተክልን እየገነደሰባቸው ተስፋ ወደ መቁረጥ እየገቡ ስለሆነ ይሄን ችግር መፍታት ተገቢ ነው፡፡

ረ. በተለያየ ድርቅ እና የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የመኖ ችግር ከፍተኛ በመሆኑ የእንስሳት ቁጥር እየቀነሰ ነው፡፡ ስለዚህ ለመኖ አቅርቦት እና ማስፋፋት ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው፡፡

# 11 የምርጥ ተሞክሮ ስራ በምስል



የዋህዲስ ሙዝ



በኮነባ ከተማ የሚገኘው የአቶ ዓሊደራ እርሻ



በዋህዲ የሚገኘው የወጣት ከድር እርሻ



በበልበል ቀበሌ የሚገኘው … እርሻ እና ችግኝ ማጓጓዝ



በፈረስ ደግ የሚገኝ የሼክ ኢብራሂም የሳር ምርት





በወርሃዊ የእርሰበርስ የመማማሪያ ጉብኝት ተሳታፊዎች በከፊል



የከፊል አርብቶ አደሮች የመስክ ጉብኝት ተሳታፊዎች

ፋጣሪ በሌላ ልማት ቦታ ላይ ለመገናኘት ያብቃን፡፡

# ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም

ፔለም ኢትዮጵያ የአባል ድርጅቶቹ አቅም በማሳደግ እርሰበርሳቸው እንዲተሳሰሩና እንዲገናኙ በማድረግ በዘላቂ ግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ ፔለም ኢትዮጵያ በአገራችን ውስጥ የሃገሪቱ ህዝብ የመቀለብ ሸክም እና ሀላፊነት በአርሶአደሮች አርብቶ አደሮች ትክሻ ላይ ነው ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ አርሶ እና አርብቶ አደሮቻችን ምርታማነትና ውጤታማነት ካላሻሻልን የአገሪቱ ልማት ከቶውን ማረጋገጥ የሚታሰብ አይሆንም ይላል፡፡ የአርሶአደሮችና አርብቶአደሮች ማህበረሰብ እጆቻቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም፡፡ ይልቁንስ ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሚሆኑ የተለያዩ ዘዴዎች በግልም ይሁን በጋራ እንደማህበረሰብ ሲሞክሩ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለጥረቶቻቸው እና አገር በቀል ለሆኑት ፈጠራዎቻቸው የሚገባቸውን ያክል በቂ ትኩረት እና እውቅና አላገኙም፡፡

ስለዚህ ፔለም ኢትዮጵያ የጋራ ጥረቶቻችን በማስተባበር፣ የተለያዩ ዘዴዎችና ልምዶችን በመጠቀም አባል ድርጅቶቻችን በአገሪቱ የልማት ስራዎች እንዴት መከወን እንዳለባቸው ተፅእኖ ለመፍጠር የሚያስችለው የተቀናጀ አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት አንዱ ነው፡፡ ለዚሁም ነው ይህ መፅሃፍ የያዘው መልካም ተሞክሮ በኮነባ ወረዳ (አፋር) ላይ ውጤታማ በሆነ ፕሮጀክት ላይ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ዳቦ ለአለም (ብሬድ ፎር ዘ ዎርልድ) በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በዚሁ ፕሮጀክት ላይ የተጠቃሚዎች ኑሮ በማሻሻል በኩል እንዲሁም ይህ ስራ በስኬት እንዲጠናቀቅ ለማስቻል ላበረከተው የገንዘብ ድጋፍ ፔለም ኢትዮጵያ ታላቅ ምስጋና ያቀርባል፡፡

PELUM ASSOCIATION
Brot für die Welt

MCMDO
Meseret Humanitarian Organization
MELCA-Ethiopia

APDA
ISD INSTITUTE FOR SUSTAINABLE DEVELOPMENT
PESTICIDE ACTION NEXUS ASSOCIATION (PAN-Ethiopia)

SEND A COW
RiftValley Initiative For Rural Advancement
Agri Service Ethiopia
አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ